ከሙስና የጸዱች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

ቅፅ 01 ቁጥር 24 ሰኔ 30 /2016/ ዓ.ም

# "ሙስና ነቀርሳ ነው፤ ሀገርን ይበላል!"



ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በ36ኛዉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መደበኛ ስብሳበ ላይ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን በሚመለከት የተለያዩ ነጥቦችን አንስተዋል፡፡ "ሌብነት ነቀርሳ ነው፤" ሀገርን ይበላል፤ ትንሽም ሆነ ትልቅ ሌብነት መጥፋት አለበት፥ ለዚህም ነው መንግስት የህግ ማሻሻያዎችን እያደረገ ያለው ብለዋል፡፡ የንብረት ማስመለስ ረቂቅ አዋጅም ይህን ታሳቢ ያደረገ እንደሆነም ገልፀዋል፡፡

የንብረት ማስመለስ አዋጅ ንፁሃንን ለመንካት ሳይሆን ሌቦችን ለመቅጣት ያለመ መሆኑን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፥ ጤነኛ የገንዘብ ዝውውር እንዲኖር እና ኢኮኖሚያችን እንዲረጋጋ አዋጁ አስፈላጊ ነው፡፡ አላግባብ ገንዘብ የሰበሰቡ ሰዎች በገንዘባቸው ማሕበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀም ሀሰተኛ መረጃዎችን እንደሚያሰራጩ ጠቅሰው፣ ሰዎች በነዚህ መረጃዎች ከመደናገር መሬት ላይ ያለውን እውነታ መረዳት እንዳለባቸው ተናግረዋል፡፡

የተደራጀ መንግሥታዊ ሌብነት አለመኖሩን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ማንኛውም የመንግሥት አካል በሌብነት ውስጥ መገኘቱን ማስረጃ የሚያቀርብ ካለ እርምጃ ለመውሰድ አናመነታም ነው ያሉት፡፡ አዋጁ በአየር ላይ የሚንቀሳቀስ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ስላለ ለማጣራት ስንሞክር ስለ ጉዳዩ ምንም በማያውቁ አርሶ አደሮች ስም እንደሚነገድ ለማረጋገጥ ስለተቻለ ተወያይተን ህግ ስናወጣ ግለሰቦችን ለማጥቃት ነው የሚሉ ግለሰቦች ተስተውለዋል ሲሉ ተደምጠዋል፡፡

ወደ ገጽ 4 ዞሯል..

በውስጥ ገፆች

የተመዘበረ ሀብት ለማስለመስ ዓለም አቀፍ ትብብር እና ቅንጅት እንደሚያስፈልግ ተገለፀ

ገጽ 8

የንብረት ማስመለስ ረቂቅ አዋጅ በወንጀል ድርጊት ተጠቃሚ መሆንን የሚያስቀርና ነው

ገጽ 7

# ዲጂታል የሙስና መጠቆሚያ መተግበሪያ ጥቅም ላይ ዋለ



ኮሚሽኑ ለፌደራል፣ ለክልል እና ለከተማ አስተዳደር የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች እንዲሁም ለፌደራል ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ሥራ አስፈፃሚዎች አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ባለማው ብሔራዊ የሙስና መጠቆሚያ ዲጂታል መተግበሪያ ስርዓት /National Corruption Reporting System - NCRS/ በአዳማ ከተማ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በመድረኩ የተገኙት የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ክቡር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር) ሀገር አቀፍ የሙስና ትግል በማካሄድ የሕብረተሰቡን ተሳትፎ ማበረታታት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡ በቀጣይም የሙስና ወንጀል ጥቆማ በአገር አቀፍ ደረጃ በለማው ዲጂታል መተግበሪያ እንደሚከናዎን ገልፀዋል፡፡ ክቡር ኮሚሽነሩ አክለውም በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጀመረውን የሙስና ትግል ያለኅብረተሰብ ተሳትፎ ከግብ ማድረስ ስለማይቻል ትግሉን በቴክኖሎጂ መደገፍ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡ ዲጂታል መተግበሪያው ዜጎች በየተቋማቱ አገልግሎት ለማግኘት ሄደው ለብልሹ አሰራር ሲጋለጡ እንዲሁም የሙስና ተግባር ሲያጋጥማቸው በስልካቸው ጥቆማ የሚሰጡበት ቴክኖሎጂ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ የአርተፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ያለማው የጥቆማ መቀበያ ሶፍትዌር ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመታገል ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በዋናነት ሕብረተሰቡ ግንባር ቀደም ተሳታፊ እንዲሆን ማስቻል ይኖርብናል ያሉ ሲሆን፥ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን የማጋለጥ ኃላፊነት ለሕግ አካላት

ወደ ገጽ 4..

# የኢትዮጵያ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች አገርዓቀፍ ፎረም 10ኛ ዙር የትስስር ጉባኤ መድረክ ተካሄደ





በውይይት መድረኩ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች በ2016 በጀት ዓመት በትውልድ ሥነምግባር ግንባታ፣ በሙስና መከላከል እና በተቋማዊ አቅም ግንባታ ዘርፎች በዘጠኝ ንዑስ ፕሮግራሞች የተከናወኑ ስራዎች እንዲሁም የ2017 በጀት ዓመት እቅድ ቀርቦ ውይይት በማካሄድ የጋራ መግባባት ተፈጥሯል፡፡

በመድረኩ የተገኙት የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ክቡር ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር) እንደገለፁት በበጀት ዓመቱ በትውልድ ሥነምግባር ግንባታና በሙስና መከላከል ሥራዎች ላይ አበረታች ውጤት መመዝገቡን ተናግረዋል፡፡ በቀጣይ በጀት ዓመትም በሀገር አቀፍ ደረጃ በትውልድ ሥነ ምግባር ግንባታ፣ በሙስና መከላከል እና በተቋማዊ አቅም ግንባታ ዘርፎች በዘጠኝ ንዑስ ፕሮግራሞች ላይ ትኩረት በማድረግና ቅንጅታዊ አሰራርን በመከተል መስራት ይኖርብናል ብለዋል፡፡



ኮሚሽነሩ አክለውም በጥናት በተለዩና ለብልሹ አሰራር ተጋላጭ የሆኑ ተቋማትን በመለየት በትኩረት መስራት እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡ አሰራሮቻችን መገምገም የሚያስችል የክትትል ሥርዓት በመዘርጋት ለሀገር የሚጠቅም ተግባር እንደሚሰራም ተናግረዋል፡፡

የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር ክቡር እሸቴ አስፋው በበኩላቸው በሀገር ደረጃ የሙስና ጥቆማን መሰረት በማድረግ የተሻለ ስራ መሰራቱን ገልፀው፥ በፌደራል ደረጃ በበጀት ዓመቱ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ በሆኑ 25 ዘርፎች ላይ የሙስና ተጋላጭነት ጥናቶች ማካሄድ ተችሏል ብለዋል፡፡ የአሰራር ብልሹነትና የሥነ ምግባር ጉድለቶችን ጨምሮ ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ መንስኤዎችን በጥናት በመለየት ተቋማቱ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ግብረ መልስ መስጠቱንም አመልክተዋል፡፡

ም/ኮሚሽነሩ አክለውም በቀጣይም ተቋማት ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን መከላከል የዋና ስራቸው አካል በማድረግ እንዲተገብሩ ይደረጋል ብለዋል፡፡ በ2017 በጀት ዓመትም በክልል እና በከተማ አስተዳደር የድጋፍና ክትትል ሥርዓትን በመዘርጋት በትኩረት እንደሚሰራ ገልፀው፥ ሁላችንም የትብብር መንፈስ በመላበስና ቅንጅታዊ አሰራርን በመከተል የተሻሉ ተግባራትን መስራት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡

በጉባኤው የጋራ የአቋም መግለጫ ማስቀመጥ የተቻለ ሲሆን፤ በመድረኩም የፌደራል፣ የክልል እና የከተማ አስተዳደር የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ዋና እና ምክትል ኮሚሽነሮች፣ የማኔጅመንት ካውንስል አባላት እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተሳትፈዋል፡፡

# ጥፋተኛ ሆነው የተገኙ ዳኞችና ተሿሚዎች ላይ የቅጣት ውሳኔ ተላለፈ

የሐረሪ ክልል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የሥነምግባር ጉድለት ክስ በተመሰረተባቸው የፍርድ ቤቱ ዳኞች እና የጉባኤ ተሿሚዎች ላይ የስራ ስንብት እና የደሞዝ ቅጣት ውሳኔ አስተላልፏል፡፡ ጉባኤው ባለፉት ወራት ከማህበረሰብ የቀረቡ ቅሬታዎችንና የምርመራ ውጤቶችን መነሻ በማድረግ የፍርድ ቤቱ ዳኞች ሥነምግባር ደንብን በመተላለፍ የዲሲፕሊን ጥፋት በፈፀሙ ዳኞችና የጉባኤ ተሿሚዎች ላይ ክስ ተመስርቶ ለክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የቀረበ መሆኑን አስታውሷል፡፡ ጉባኤው የቀረበለትን የሥነምግባር ጉድለት ክስና ማስረጃዎች ከህጉ አንፃር አገናዝቦ በመመርመር ከቀረቡለት 13 ክሶች መካከል 10 ክሶች ላይ ጥፋት መፈፀሙን በማረጋገጥ ክስ የቀረበባቸው 5 ዳኞች እና 4 የጉባኤ ተሿሚዎች ጥፋተኛ ናቸው ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ እንዲሁም 3 ክሶች በቂ ማስረጃ ያልቀረበባቸው በመሆኑ ውድቅ ያደረጋቸው መሆኑን አስታውቋል፡፡



በዚህም ጥፋተኛ የተባሉ 1 የሸሪአ ፍርድ ቤት ዳኛና 2 ተሿሚዎች ከስራ እንዲሰናበቱ የተወሰነ ሲሆን፣ 1 የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ፣ 2 የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞችና 1 ዳኛ በአራት ወር ደሞዝ እንዲቀጡ፣ 1 የተከሳካይ ጠበቆች አስተባባሪ ከደሞዝና ደረጃ ዝቅ እንዲል እና 1 ባለሙያ የሶስት ወር ደሞዝ እንዲቀጡ ጉባኤው የቅጣት ውሳኔ አስተላልፏል፡፡ የክልሉ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶች ማኔጅመንት ባከናወነው ግምገማ ክፍተት አለባቸው ተብለው በተለዩ መደቦች ላይ ለዳኞች እና ለጉባኤ ተሿሚዎች የስራ ድልድል አከናውኗል፡፡

በዚሁ መሠረት በቀረበባቸው የዲሲፕሊን ክስ ጥፋተኛ ተብለው የቅጣት ውሳኔ የተላለፈባቸዉ 3 ዳኞች ከዳኝነት ስራ ተነስተው በሌሎች የአስተዳደር ስራዎች ላይ እንዲመደቡ መደረጉም ተጠቁሟል፡፡ በቀጣይም የተጠያቂነት ስርዓትን በማጠናከር ከመሠረታዊ የብቃት ማነስና ከሥነምግባር ብልሹነት ጋር ተያይዞ የሚስተዋሉ ችግሮችን ህግና ስርዓትን ተከትሎ እንዲቀረፉ በማድረግ የማጥራቱን ስራ ለመተግበር ጉባኤው በቁርጠኝነት እንደሚሰራ መገለጹን የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ መረጃ ያመላክታል፡፡

ከሙስና የፀዳች ኢትዮጵያ!

# የሚዲያ ተቋማትና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የፀረ-ሙስና ፎረም ተመሰረተ





የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከሚዲያ ተቋማት እና ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር የትውልድን ሥነምግባር ለመገንባትና ሙስናን መከላከል የሚያስችል የፎረም ምስረታ አካሄዷል፡፡ በመድረኩ የተገኙት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ም/ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ አዝመራ አንደሞ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚዲያ ተቋማትና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሚናቸው የጎላ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የተከበሩ አቶ አዝመራ አንደሞ አክለውም ሀገራችን ኢኮኖሚያዊ እድገቷና ሰላሟ የተረጋጋ እንዲሆን ሌብነት ላይ ትኩረት አድርገን ልሰራ ይገባል ብለዋል፡፡ ለዚህም የሚዲያ ተቋማትና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የማህበረሰብ ግንዛቤ መፍጠር ላይ በትኩረት ሊሰሩ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና መከላከል ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር እሸቴ አስፋው በበኩላቸው ኢትዮጵያን የአፍሪካ የብልፅግና ተምሳሌት ለማድረግ ሙስና እና ብልሹ አሰራር ላይ ትኩረት አድርገን መስራት አለብን ብለዋል፡፡ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ከምንጊዜውም በላይ መዋጋት የሚያስፈልግበት ወቅት ላይ እንገኛለን ያሉ ሲሆን፥ ለዚህም ያግዝ ዘንድ ኮሚሽኑ የመንግስት አሰራሮችን በማሻሻል ረገድ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራበት እንደሚገኝ አመላክተዋል፡፡ ይሁን እንጂ የሙስና ወንጀል እያደረሰ ካለው ጉዳት አኳያ በአንድ ተቋም ብቻ መቆጣጠርና መከላከል በቂ ሆኖ ባለመገኘቱ ከተባባሪ አካላት ጋር በቅርበት ለመስራት ፎረም ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

አሁን የተመሰረተው ፎረም ተቀራርቦ በጋራ ከመስራት አንፃር እንዲሁም ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ነቅሶ ከማውጣት አኳያ ሚናው የጎላ ይሆናል ብለዋል፡፡ መገናኛ ብዙሃን ያላቸውን አቅም በመጠቀም ሙስናን በመከላከልና ወንጀለኞችን በማጋለጥ ረገድ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ የፎረሙ ሚና የጎላ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመዋጋት የጋራ ጥረትን ይጠይቃል ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ፥ በዚህ ሂደት ውስጥም የሲቪክ ማኅበረሰብ ድርጅቶችና የሚዲያ ተቋማት ከፍተኛ አበርክቶ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው አሳስበዋል፡፡ ፎረሙ እንደ ሀገር ሙስናን ለመከላከልና ተጠያቂነትን ለማስፈን እየተደረገ ያለውን ጥረት ከማጠናከር ባሻገር የምርመራ ጋዜጠኝነትን ውጤታማ ለማድረግ ታልሞ የተቋቋመ ስለመሆኑም ገልፀዋል፡፡

የመገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ጽህፈት ቤት ኃላፊ ወ/ሮ የሺወርቅ ግርማ በበኩላቸው የመገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን በአዋጅ ከተሰጣቸው ተግባራት መካከል በሥነምግባር የታነጸ፣ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን የሚፀየፍ ዜጋ ማፍራት ነው ብለዋል፡፡ ወ/ሮ የሺወርቅ ግርማ አክለውም የሚዲያ ተቋማት በሙስና መከላከል ትግል ውስጥ ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል ያሉ ሲሆን፥ ባለስልጣኑ ይህ ፎረም ሲቋቋምም ተቋማቱ በፀረ-ሙስና ትግል ሂደት ውስጥ የበኩላቸውን እንዲወጡ የማስተባበርና የማቀናጀት ተግባር ይፈፅማልም ብለዋል፡፡

በመድረኩ የተገኙት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ሳምሶን ቢራቶ እንደገለፁት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ከተቋቋመበት አላማ አንዱ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን መከላከል መሆኑን ገልፀው፣ መስሪያ ቤታችንም ችግር የሚፈጥሩ ግለሰቦችን እርምጃ እየወሰደም፣ እያስወሰደም እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡ የሀገራችን እድገትና ብልፅግና ጉዞ ውጤታማ ለማድረግ ሙስና እና ብልሹ አሰራር ላይ ኃላፊነት በመውሰድ በቁርጠኝነት መታገል ይኖርብናል ብለዋል፡
፡

የኮሚሽኑ የሥነምግባር ግንባታና የፀረ-ሙስና ባለድርሻ አካላት ተጠባባቂ መሪ ስራ አስፈፃሚ አቶ ከፍያለው አለሙ ለውይይት መድረኩ የሚሆን የሥነምግባር ግንባታና የፀረ-ሙስና ፎረም ፕሮቶኮል ሰነድ አቅረበው ውይይት ተደርጎበታል፡፡ በፎረሙ ማቋቋሚያ መርሃ ግብር ላይም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ አዝመራ አንደሞን ጨምሮ የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራሮች፣ የሚዲያ ተቋማትና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አመራሮችና ተወካዮች ተገኝተዋል፡፡

ከዚህ በፊት የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከሚዲያ ተቋማት እና ሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች የስራ ኃላፊዎች ጋር በቅድመ ፎረም ምስረታ ዙሪያ ውይይት ማካሄዱ ይታወቃል፡፡

# ክቡር ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር) ከተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም (UNDP) ተወካዮች ጋር በጋራ በሚሰሩባቸው ጉዳዮች ላይ ውይይት አደረጉ



የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ክቡር ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር) ከተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም (UNDP) ተወካዮች ጋር በጋራ በሚሰሩባቸው ጉዳዮች ላይ ውይይት አድርገዋል፡፡ ውይይቱ የሁለቱ ተቋማት የአቅም ግንባታና የፀረ-ሙስና ሥራውን አጠናክሮ ለመቀጠል በተለዩ የትኩረት መስኮች እና የተግባራት መርሃግብር ዝግጅት የጋራ ግንዛቤ ለመፍጠር ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

ከገጽ አንድ የዞረ...

## “ሌብነት ነቀርሳ ነው....

በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቂት ግለሰቦች በህገ ወጥ መንገድ በርካታ ቢሊዮን ብር ያንቀሳቅሳሉ፤ ይህን መጠየቅ የሚችል ህግ አልነበረንም። የንብረት ማስመለስ አዋጁ ይህን ችግር በመቅረፍ የህግ ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ እንደሆነም ገልፀዋል። ነገር ግን አዋጁ ያጠቃናል ያሉ ሌቦች ከወዲሁ የተሳሳተ መረጃ በማሰራጨት ህዝብን ለማደናገር እየሞከሩ ነው። በመሆኑም ሌብነትን በመታገል ረገድ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በተግባር የተጨበጠ ስራ ማከናወን አለበት ብለዋል።

ሙስና ፖለቲካዊም፣ ኢኮኖሚያዊም አንድምታ አለው፥ ሌባ ሰው ራሱንም፣ ቤተሰቡንም አይጠቅምም። ሌብነት ጉዟችንንም ያደናቅፋል ብለዋል። የተቋማት ሪፎርምና የህግ ማሻሻያዎች እየተደረጉ ያሉት መታረም ያለባቸው ጉዳዮች ስላሉ መሆኑንም ጠቁመዋል። አሰራሮቻችንን



ከገጽ አንድ የዞረ...

## ዲጂታል የሙስና መጠቆሚያ....

ብቻ የሚተው ሳይሆን ሁሉም ዜጋ የጉዳዩን አስከፊነት በመረዳት ለሃገር አቀፍ የሙስና ትግል የበኩሉን ድርሻ መወጣት ይጠበቅበታል ሲሉ አሳስበዋል።

የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር ክቡር እሸቴ አስፋው በበኩላቸው ኢትዮጵያ የአፍሪካ የብፅግና ተምሳሌት ለማድረግ ሙስና እና ብልሹ አሰራር ላይ ትኩረት በመስጠትና በቅንጅት መስራት ይኖርብናል ብለዋል። ሙስና የሀገራችን የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና የሰላም ቀውስ እየፈጠረ በመሆኑ በጋራ ልንታገለው ይገባል ያሉ ሲሆን፥ ለዚህም የበኩላችሁን ልትወጡ ይገባል በማለት መልዕክት አስተላልፈዋ።

ስልጠናውን የሰጡት የአርተፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ታዬ ግርማ (ዶ/ር) ዜጎች በተለያዩ የመንግስት ተቋማት ላይ በሚያገኟቸው አገልግሎቶች ላይ ያላቸውን አስተያየት ወይም የእርካታ መጠንና በአገልግሎት ሂደት የሚገጥማቸው የመልካም አስተዳደር ችግርን የሙስና ጥቆማ ሶፍትዌሩን በመጠቀም በየትኛውም ቦታና በፈለጉበት ሰዓት ጥቆማ ወይም አስተያየታቸውን መስጠት እንደሚችሉ አብራርተዋል። የስልጠናው ተሳታፊዎች የተለያዩ ሀሳብና አስተያየቶች እንዲሁም ጥያቄዎች አንስተው ከመድረኩ ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶበታል።



# በሀገራዊ የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ረቂቅ ፖሊሲ ዙሪያ ውይይት ተካሄደ

የአብክመ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በሀገራዊ የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ረቂቅ ፖሊሲ ዙሪያ ከክልልና ዞን ከተወጣጡ የሚመለከታቸው አካላት በተገኙበት ውይይት አካሂዷል። የኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ዳይሬክተር አቶ ፋሲል አለኸኝ የረቂቅ ፖሊሲውን ሰነድ በመድረኩ ያቀረቡ ሲሆን፥ የፖሊሲው መነሻ ሀሳቦች፣ አስፈላጊነት፣ መርሆዎች፣ የፖሊሲው ዋና ዋና ጉዳዮች እና አቅጣጫዎች፣ የፖሊሲው ቁልፍ የውጤት መስኮች፣ ፖሊሲዉን የማውጣት ስልጣንና ኃላፊነት እንዲሁም የፖሊሲው የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎችን በዝርዝር ማየት ተችሏል።

በመድረኩ የተገኙት የክልሉ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሀብታሙ ሞገስ እንደገለፁት የፖሊሲው መውጣት ለተቋማችን ነፃና ገለልተኛ ሁነን በቆራጥነት ለመስራት በጣም አስፈላጊ መሆኑን ተናግረው፥ የውይይቱ ዓላማ በዋናነት ለረቂቅ ፖሊሲው ግብዓት የሚሆኑ ሀሳቦችን ማሰባሰብ ነው ብለዋል። ኮሚሽነሩ አክለውም ፖሊሲው በስራ ላይ ለረዥም ጊዜ የሚቆይ በመሆኑ ከሌሎች ተቋማት ፖሊሲዎች ጋር ባልተጣረሰ መልኩ በረቂቅ ፖሊሲው ይዘት ላይ ብቻ በማተኮር በየተቋማችሁ በመወያየት በፖሊሲው መካተት ያለባቸውን ሀሳቦች በማሰባሰብ ፖሊሲዉ እንዲዳብር ተጨማሪ ግብዓት መስጠት እንዳለባቸው አሳስበዋል።

የውይይቱ ተሳታፊዎች በበኩላቸው ተቋሙ ፖሊሲ እንዲኖረው መደረጉ እጅግ ጠቃሚ መሆኑን ገልፀው፥ በረቂቅ ፖሊሲው መካተትና በትኩረት ቢታዩ ያሏቸውን ሀሳቦችን አስተዋል። ለተነሱ ሀሳብና አስተያየቶች በመድረኩ በተገኙት የኮሚሽኑ አመራሮች ምላሽ መሰጠቱ ተገልጿል።በውይይት መድረኩ የኮሚሽኑ አመራርና ሰራተኞች፣ የክልል ቢሮዎች እና የዞን የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ዳይሬክተሮችና ባለሙያዎች ተሳትፈዋል። በተያያዘ መረጃ የአብክመ የሥነምግባር



እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በሀገራዊ ከልማት ድርጅቶች ከመጡ የግዥ፣ የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክተሮችና ረቂቅ ፖሊሲ ዙሪያ ከክልል ቢሮዎችና ኦዲተሮች ጋር ውይይት አካሂዷል።



## ምክር ቤቱ የንብረት ማስመለስ ረቂቅ አዋጅን ለሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴ መራ

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

በተካሄደው 31ኛ መደበኛ ስብሰባ የንብረት ማስመለስ ረቂቅ አዋጅን መርምሮ ለሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴ መርቷል:: ምክር ቤቱ በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰልና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የቀረበ ረቂቅ አዋጅንም መርምሮ ለዝርዝ እይታ ወደሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መርቷል:: በምክር ቤቱ የመንግሥት ረዳት ተጠሪ ሚንስቴር ዴኤታ የተከበሩ ወ/ሮ መሰረት ሀይሌ ረቂቅ አዋጁን አስመልክቶ አጭር ማብራሪያ ያቀርቡ ሲሆን፤ የንብረት ማስመለስ ረቂቅ አዋጅ ዓላማ የወንጀል ፍሬ የሆኑ ንብረቶችንና ገንዘቦችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመያዝ ወይም ለመውረስ እንዲሁም ለማስተዳደር የሚያስችል መሆኑን ገልፀዋል:: ረቂቁ ማንኛውም ሰው በህገ ወጥ ድርጊት ጥቅም እንዳያገኝ ለማድረግ የሚያስችል የንብረት ማስመለስና ማስተዳደር ስርዓት ለመዘርጋት እንደሚያስችል ተጠቁሟል::

## የኮሚሽኑ አመራሮች በኦስትሪያ ቬና የተመዘበረ ሀብት ማስመለስ ላይ ባተኮረ የባለሙያዎች ቡድን መድረክ ላይ ተሳተፉ



የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነሮች በኦስትሪያ ቬና፥ የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ስምምነት ስር በሚካሄደው ዓለምአቀፍ ትብብር ለማጠናከር እና ከሀገር የሸሸ የሀብት ማስመለስ ላይ ትብብር ዓላማ ባደረገው 18ኛው መድረክ ላይ ተካፍለዋል::

## ከቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ የግንባታ ግዢ ጋር ተያይዞ የተከሰሱ 8 ግለሰቦችና 1 ድርጅት ጥፋተኛ ተባሉ

ከቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ የግንባታ ግዢ ጋር ተያይዞ በሙስና ወንጀል የተከሰሱ ስምንት ግለሰቦች እና አንድ ድርጅት በሌሉበት ጥፋተኛ ተባሉ:: ሌሎቹ የቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ የቀድሞ ፕሬዚዳንት ጫላ ዋታ (ዶ/ር) ጨምሮ ሰባት ተከሳሾች በ1ኛ ክስ እንዲሁም 2ኛ እና 3ኛ ክስ በአንድ ክስ ተጠቃሎ እንዲከላከሉ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 4ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ብይን ሰጥቷል:: በተጨማሪም ፍርድ ቤቱ 1ኛ ተከሳሽ ጫላ ዋታ (ዶ/ር) የቀረበባቸው በህገወጥ መንገድ የተገኘ ንብረትን ወይም ገንዘብን ህጋዊ አድርጎ በማቅረብ ምንጩን ደብቀዋል ወይም አሽሽተዋል በሚል የቀረበባቸውን 4ኛ ክስን በሚመለከት ወደ ባለቤታቸው ሂሳብ ገንዘብ ማስገባታቸው አሽሽተዋል ለማለት አያስችልም በሚል ነጻ ተብለዋል::

ሆኖም ግን ገንዘብ ገቢ ሆኖላቸዋል የተባሉት የ1ኛ ባለቤት የሆኑት 15ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ፀሃይ ሀይሉ ግን ወደ ሂሳባቸው የገባውን ገንዘብ ለማሸሽ ቤት በመግዛት ለግል ጥቅም አውለውታል በሚል በቀረበባቸው ማስረጃ መሰረት በሌሉበት ጥፋተኛ ተብለዋል:: የፍትህ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ የሙስና ወንጀል ክስ አቅርቦባቸው ከነበሩ ሁለት የኮንስትራክሽ የግል ድርጅቶችንና 16 ግለሰቦች መካከል ያለመከሰስ መብታቸው በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የተነሳው የቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ የቀድሞ ፕሬዚዳንት ጫላ ዋታ (ዶ/ር)፣ የዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ታምሩ ኦኖሌ፣ የአስተዳደር እና የተማሪዎች አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ሮባ ደንቢ (ዶ/ር)፣ የቢዝነስና ተቋማዊ ልማት ም/ፕሬዚዳንት አብርሃም ባያብል (ኢ/ር)፣ የግዢ ዳይሬክተር የነበሩት ሊበይ ገልገሎ፣ የግዢ ዳይሬክተር የሆኑት ቦሩ ህርቦዬ እንዲሁም የዩኒቨርሲቲው መምህርና የቢኤች ዩ አማካሪ ለታ ድሪባ ጨምሮ ጠቅላላ ስራ ተቋራጮችና የቢዳሩ ኮንስትራክሽን ስራ አስኪያጆችም ይገኙበታል::

ዐቃቤ ሕግ ከ1ኛ እስከ 6ኛ ተራ ቁጥር ያሉት ተከሳሾች ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ የዩኒቨርሲቲው አመራርና የማኔጅመንት አባል በመሆን ሲሰሩ የመንግስት ግዢ መመሪያን በመተላለፍ በሰኔ 10 ቀን 2012 ዓ.ም ከሌሎች ተከሳሾችና ከስራ ተቋራጭ ጋር ያለአግባብ ግዢ በመፈጸም በመንግስት ላይ 195 ሚሊየን 52 ሺህ 812 ብር ከ81 ሳንቲም ጉዳት አድርሰዋል የሚል እና የ14 ተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎችን ግዢ መፈጸም እና በዚህ ማሽነሪና ተሽከርካሪ ግዢ ደግሞ 12ኛ፣ 13ኛ፣ 14ኛ፣ 16ኛ ተከሳሾች ጥቅም አግኝተውበታል በማለት በዋና ወንጀል አድራጊነትና በልዩ ወንጀል ተካፋይ በመሆን የተከሳሽ የተሳትፎ ደረጃቸውን ጠቅሶ ስልጣንን ያለአግባብ መገልገል ተደራራቢ የሙስና ወንጀል ሰፋ ያለ ዝርዝር ክስ አቅርቦባቸው ነበር::

በዚህ መልኩ የተመሰረተባቸው ዝርዝር ክስ በችሎት ለቀረቡ ከ1ኛ እስከ 7ኛ ተራ ቁጥር ለተጠቀሱ ተከሳሾች እንዲደርስ ከተደረገና በችሎት ክሱ በንባብ ከተሰማ በኋላ ተከሳሾቹም በጠበቆቻቸው አማካኝነት የቀረበባቸው ክስ ዝርዝር ፍሬ ነገሩ እንዲሻሻልላቸው የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ አቅርበዋል:: ከብይኑ በኋላ ከ1ኛ እስከ 7ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱ ተከሳሾች በማረሚያ ቤት ሆነው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ በተሰጠ ትዕዛዝ መሰረት ከማረሚያ ቤት ቀርበው በክስ ዝርዝሩ ላይ የተጠቀሰውን የወንጀል ድርጊት አለመፈጸማቸውን ገልጸው የዕምነት ክህደት ቃላቸውን ሰጥተዋል:: ከዚህም በኋላ ዐቃቤ ሕግ ከ10 በላይ የሰውና የሰነድ ማስረጃ ያቀረበ ሲሆን፣ ፍርድ ቤቱ ዐቃቤ ሕግ ያቀረባቸውን የምስክር ቃል መርምሮ በቀጠሮው ብይን ሰጥቷል:: በዚህም ከቀረቡባቸው ክሶች መካከል በ1ኛ ክስ ላይ ከ1ኛ እስከ 7ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱ ተከሳሾች እንዲከላከሉ የተባሉ ሲሆን በዚሁ ክስ የተካተተው 8ኛ ተከሳሽ በሌለበት ጥፋተኛ ተብሏል:: በሌላ በኩል ችሎቱ የተሽከርካሪ ግዢን የሚመለከተው 3ኛው ክስ የግንባታ ግዢ ላይ ከሚያተኩረው ከ2ኛ ክስ ጋር እንዲጠቃለል በማለት በዚህ ክስ ከ1ኛ እስከ 6ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ተከሳሾች እንዲከላከሉ ብይን ሰጥቷል::

በዚሁ በተጠቃለለው ክስ የተካተቱ በሌሉበት ጉዳያቸው የታዩት ከ8ኛ እስከ 13ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱ ተከሳሾች እንዲሁም 16ኛ እና 18ኛ ተከሳሽ በሌሉበት የጥፋተኝነት ፍርድ ተሰጥቶባቸዋል:: የተሽከርካሪና የማሽነሪ ግዢን በሚመለከተው ክስ ላይ ተካተው የነበሩት 14ኛ ተከሳሽ አይመን አብዱላሂና እና 17 ተከሳሽ አረብ ኮንስትራክሽን የግል ድርጅት በሚመለከት በቂ ማስረጃ ያልተሰማባቸው መሆኑ ተጠቅሶ ነጻ ተብለዋል::

በተጨማሪም ፍርድ ቤቱ በ4ኛ ክስ ከባለቤታቸው ጋር የተከሰሱት 1ኛ ተከሳሽ ጫላ ዋታ ዶ/ር የቀረበባቸው በህገወጥ መንገድ የተገኘ ንብረትን ወይም ገንዘብን ህጋዊ አድርጎ ማቅረብ ተብሎ የተመሰረተባቸው ክስ ወደ ባለቤታቸው ሂሳብ ገንዘብ ማስገባታቸው ብቻ አሽሽተዋል ለማለት አያስችልም በማለት ነጻ ተብለዋል:: ሆኖም ግን ገንዘብ ገቢ ሆኖላቸዋል የተባሉት የ1ኛ ተከሳሽ ባለቤት የሆኑት 15ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ፀሃይ ሀይሉ ግን ወደ ሂሳባቸው የገባውን ገንዘብ ምንጭ ለማሸሽ ቤት በመግዛት ለግል ጥቅም አውለውታል በሚል በቀረበባቸው ማስረጃ መሰረት በሌሉበት ጥፋተኛ ተብለዋል:: ፍርድ ቤቱ ተከላከሉ የተባሉ ሰባት ተከሳሾችን የመከላከያ ማስረጃ ለመጠባበቅ ከሐምሌ 22 ጀምሮ ለአምስት ቀናት ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቷል::

# የኢንቨስትመንት ስራዎች አፈፃፀም እና የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትና ስርጭት ሂደት ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ያለዉ የተጋላጭነት ጥናት ግኝት ላይ ውይይት ተካሄደ

የሲዳማ ክልል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በክልሉ የኢንቨስትመንት ስራዎች አፈፃፀም እና የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትና ስርጭት ሂደት ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ያላቸዉን ተጋላጭነት ለመለየት በተደረጉ የጥናት ግኝት ላይ ጥናቶቹን ወደ ተግባር ለማሸጋገር ከባለድርሻ አካላት ጋር ዉይይት ተካሄዷል።

በመድረኩ የተገኙት የክልሉ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ወ/ሮ ዘላለም ለማ እንደገለፁት ኮሚሽኑ በመንግስት ተቋማት ዉስጥ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር የተጋለጡ አሰራሮችን በመፈተሽ በተሻሻሉ አሰራሮች እንዲተኩ እያደረገ ሲሰራ መቆየቱን ተናግረዋል። ኮሚሽነሯ አክለውም ጥናቶቹ የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትና ስርጭት እንዲሁም የኢንቨስትመንት ፍቃድ አሰጣጥና እድሳት ስርዓት ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ያለዉን ተጋላጭነት በመለየት ብልሹ አሰራሮችን ለማረም ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ገልፀዋል። ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን አስቀድሞ የመከላከል ተግባር በመስራት አመርቂ ለውጥ ማምጣት ተችሏል ብለዋል።

የክልሉ ብልጽግና ፓርቲ የፖለቲካና አቅም ግንባታ ዘርፍ ኃላፊ በበኩላቸው ሙስና ቀጣይነት ላለዉ የማህበራዊ ልማትና ለመልካም አስተዳደር እንዲሁም ለዴሞክራሲ ግንባታ አደናቃፊ መሆኑን ጠቁመዋል። ሙስና የተወሰነ ቡድን ብቻ የበላይነትን በመያዝ ፍትሀዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት እንዳይኖርና በዜጎች መካከል ልዩነት በመፍጠር ወደ ግጭት እንዲያመሩ የሚያደርግ መሆኑን ገልፀው፥ ለዚህም ሁሉም ዜጋ ሙስናን ለመዋጋት በሚደረግ ትግል ንቁ ተሳትፎ ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበዋል። በመድረኩ በአፈር ማዳበሪያ





እና በኢንቨስትመንት አሰራር ዙሪያ የተጠና የጥናት ግኝት የቀረበ ሲሆን፥ በአፈር ማዳበሪያ ዙሪያ ለታየዉ ሙስና እና ብልሹ አሰራር በስርጭት ሂደት ላይ የሚደረግ ክትትልና ድጋፍ በቂ አለመሆንና አቅርቦቱና ስርጭቱን ለማስፈፀም የወጣዉን መመሪያና ደንብ ስራ ላይ ማዋል አለመቻል ችግር መሆኑ ተብራርቷል። እንዲሁም በኢንቨስትመንት ዘርፉ የተጠናዉ የጥናት ግኝት በስራዎች ላይ የሚደረግ ድጋፍና ክትትል በቂ አለመሆን፣ ኦዲት የሚደረግበት ስርዓት ደካማ መሆን እና ለኢንቨስትመንት የተሰጠዉን መሬት ለሌላ አላማ ማዋልና መሸጥ እንዲሁም ለኢንቨስትመንት የሚሰጥ ፍቃድ ግልጽነትና ተጠያቂነት የጎደለዉ መሆን በዘርፉ ለታየዉ ብልሹ አሰራር መንስኤ መሆኑ ተገልጿል።

በውይይት መድረኩ ለተነሱ ሀሳብና አስተያየቶች ብሎም ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ የተሰጠ ሲሆን፥ ከተቋማት ኃላፊዎች ጋርም ጥናቱን ወደ ትግበራ ማሸጋገር የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል። በመድረኩ የክልሉ ብልጽግና ፓርቲ የፖለቲካና አቅም ግንባታ ዘርፍ ኃላፊን ጨምሮ የዞን፣ የወረዳ እና የከተማ አስተዳደር የተለያዩ ኃላፊዎችና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተሳትፈዋል።

## የኮሚሽኑ አመራሮች በሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ረቂቅ ፖሊሲ ላይ ከባለድርሻ አካላት የሥራ ኃላፊዎች ጋር ውይይት አካሄዱ






የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራሮች በሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ረቂቅ ፖሊሲ ላይ ከባለድርሻ አካላት የሥራ ኃላፊዎች ጋር ውይይት አካሄደዋል።

የውይይት መድረኩ ዓላማ በሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ረቂቅ ፖሊሲ ላይ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ተቋማትና የባለድርሻ አካላት የሥራ ኃላፊዎች ጋር በመወያየት ግብዓት ለማሰባሰብ ታሳቢ ያደረገ ነው።

በመድረኩም ረቂቅ ፖሊሲው ለሚመለከታቸው የሚዲያ ተቋማት፣ ለትምህርት ሚኒስቴርና ለትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን የሥራ ኃላፊዎች፣ ለፍትህ ሚኒስቴርና ለፌደራል ፖሊስ የስራ ኃላፊዎች እንዲሁም ፖሊሲው ቀጥታ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የሥራ ኃላፊዎች ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል።

የውይይቱ ተሳታፊዎችም ለረቂቅ ፖሊሲው ግብዓት የሚሆን ሀሳብና አስተያየት ብሎም ጥያቄ አቅርበው ከመድረኩ ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶበት የጋራ ግንዛቤ ተፈጥሯል።

## ሙስናን እንፀየፍ!



ከሙስና የፀዳች ኢትዮጵያ!

# ሴቶች ሙስናን በመከላከል በሚደረግ ተግባራት ውስጥ የድርሻቸውን ማበርከት እንዳለባቸው ተገለጸ





የጉለሌ ክፍለ ከተማ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ከ10ሩም ወረዳ ከተወጣጡ ሴቶች ጋር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መድረክ አካሄዷል፡፡ በስልጠናው ላይ በሙስና ምንነት፣ ዓይነቶች እና ሙስና በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያሚና ፖለቲካዊ የሚያደርሰው ተጽዕኖ፣ የሙስና መከላከያ ዘዴዎች እና በመከላከል ረገድ የሴቶች ሚና ምን መሆን አለበት በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ገለጻ ተደርጓል፡፡

የጉለሌ ክፍለ ከተማ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ቡድን መሪ ወ/ሮ ሙንታህ ምስጋን እንደተናገሩት ሴቶች የሥነምግባር መርሆች፣ እሴቶችን በመገንዘብና በመረዳት በሀገራችን ስር የሰደደውን ሙስናን ለመታገል የድርሻችሁን ልትወጡ ይገባል ብለዋል፡፡ ወ/ሮ ሙንታህ ምስጋን አክለውም ሴቶች በክፍለ ከተማው ግልጸኝነትና ተጠያቂነት አሰራር በማስፈን መስራት እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡ የውይይቱ ተሳታፊዎች በበኩላቸው የሀገራችን የልማት ጸር የሆነውን ሙስናን በተሰማራንበት የስራ መስክ ላይ በመታገል ሀገራችን የጀመረችውን የብልጽግና እና የልማት ጉዞ ዕውን እናደርጋለን ብለዋል፡፡

በተመሳሳይ መረጃ ለልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ለቡድን መሪዎችና ለባለሙያዎች በሥነምግባርና በመልካም አስተዳደር ዙሪያ የአቅም ግንባታ ስልጠና መሰጠቱ ተገልጿል፡፡

# የንብረት ማስመለስ ረቂቅ አዋጅ በወንጀል ድርጊት ተጠቃሚ መሆንን የሚያስቀርና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ ነው - የሕግ ባለሙያዎች



የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙት 14 ቅርንጫፎች እና ድሬደዋ በሚገኘው አንድ ቅርንጫፍ በድምሩ በአስራ አምስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሚሰሩ 725 ሰራተኞች ላይ ስራን ማዕከል ያደረገ ግምገማ አካሂዷል፡፡

በዚሁ የስራ ግምገማ ከህግና አሰራር ውጪ በተደጋጋሚ ሰነዶችን ያረጋገጡ፣ በተቋሙ ከተዘረጋው የአሰራር ስርዓት ውጪ በጥቅም ትስስር ባለጉዳይን ያስተናገዱ፣ ያለበቂ ምክንያት ተገልጋዩን ያመላለሱ፣ ያጉላሉ፣ የመንግስትን የስራ ሰዓት ያላከበሩ እና የሥራ ሰዓትን ለስራ ብቻ ማዋል ሲገባቸው ያላዋሉ እንዲሁም በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው ስድስት ወራት ዝቅተኛ የስራ አፈጻጸም ያስመዘገቡትን በመለየት አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ተደርጓል፡፡

በዚህም መሰረት፥ ከስራና ከደሞዝ የታገዱ ሰራተኞች ብዛት 11፣ በቀጥታ የዲሲፕሊን ክስ የተመሰረትባቸው 4፣ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው 38 እና የቃል ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው 25 በድምሩ በ78 ሰራተኞች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ የተወሰደባቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

ተቋሙ የተገልጋዮችን እርካታ ለማስገኘት አሰራሩን በማዘመን የምሳ ሰዓትን ጨምሮ ቅዳሜ ሙሉቀን በሁሉም ቅርንጫፎች ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ሲሆን፥ ይህንኑ አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በአዲስ አበባ ከተማ ሜክሲኮ በሚገኘው ቅርንጫፍ አስር እና በድሬደዋ ቅርንጫፍ ከጠዋቱ 2:00 - ምሽቱ 1:00 እንዲሁም ቅዳሜ ሙሉቀን በመሥራት ላይ እንደሚገኝ ገልጿል፡፡

በሰራተኞች ግምገማ ላይ በአካልና በተለያዩ መንገዶች ጥቆማ ላደረገችሁ፣ አስተያየት ለሰጣችሁ እና የተቋማችን በየደረጃዉ ያላችሁ አመራርና ሰራተኞች እንዲሁም የተቋማችን ተገልጋዮች ምስጋና ማቅረቡን ከአገልግሎቱ የፌስቡክ ገፅ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡



# የኮሚሽኑ አመራርና ሠራተኞች ከተረጂነት ወደ ምርታማነት ለተሟላ ሀገራዊ ክብር፣ ነፃነትና ሉዓላዊነት በሚል መሪ ሀሳብ ውይይት አካሄዱ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራርና ሠራተኞች ከተረጂነት ወደ ምርታማነት ለተሟላ ሀገራዊ ክብር፣ ነፃነትና ሉዓላዊነት በሚል መሪ ሀሳብ ውይይት አካሄደዋል፡፡ ለውይይት መድረኩ መነሻ የሚሆን ሰነድ በኮሚሽኑ ጽህፈት ቤት አማካሪ አቶ መስፍን በላይነህ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል፡፡ በቀረበው ሰነድ ዜጎች የተረጂነት አስተሳሰብን በማስወገድ ሀገራችንን ወደ ምርታማነት ማሻገር አማራጭ የሌለው ጉዳይ እንደሆነ





ተገንዝበው ተገቢ እቅድ ማዘጋጀትና የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እንደሚገባቸው እንዲሁም የተረጂነት አስተሳሰብን በማስወገድ የምርታማነት ደረጃን ማሳደግ ዋናው ተግባራቸው መሆን እንደሚገባ ተብራርቷል፡፡ በቀረበው ሰነድ መነሻነት የውይይቱ ተሳታፊዎች የተለያዩ ሀሳብና አስተያየት እንዲሁም ጥያቄዎች አንስተው ከመድረኩ ምላሽና ማብራሪያ በመስጠት የጋራ ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡

# ሙስናን አስቀድሞ ለመከላከል የዜጎችን ተሳትፎ ማረጋገጥ ወሳኝ መሆኑ ተገለፀ





ሙስናን አስቀድሞ ለመከላከልና ለፀረ-ሙስና ትግሉ የዜጎችን ተሳትፎ ማረጋገጥ ወሳኝ መሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ገለፀ:: ኮሚሽኑ ከከተማው ሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ጋር በመተባበር ሙስናን አስቀድሞ ለመከላከል ዜጎችን አሳታፊ ለማድረግ በሀገር አቀፍ የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ረቂቅ ፓሊሲ ላይ ከቢሮው ባለድርሻ አካላት ጋር ወይይት አድርጓል::የአዲስ አበባ ከተማ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀማል ረዲ ውይይቱን በከፈቱበት ወቅት ሙስናን አስቀድሞ ለመከላከልና ለፀረ-ሙስና ትግሉ የዜጎችን ተሳትፎ ማረጋገጥ ወሳኝ በመሆኑ በረቂቅ ፖሊሲው ላይ የውይይት መድረክ ማካሄድ ማስፈለጉን ገልፀዋል:: ኮሚሽነሩ አያይዘውም የሥነምግባር ብልሽት መኖር ለሀገረ መንግስት ግንባታ ፈታኝ መሆኑን ጠቁመው፣ እንደ ኮሚሽን ሥነምግባር ያለው ትውልድ ለማፍራት የተጀመሩ ስራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉና ጎን ለጎን በብልሹ አሰራር ውስጥ ገብተው የተገኙ ግለሰቦች ላይ አስተማሪ እርምጃ እንዲወሰዱ በማድረግ የተጠያቂነት ስርዓት እንዲሰፍን እንደሚሰራ ተናግረዋል::

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሴቶች ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ወ/ሮ ወይንሸት ታደሰ በበኩላቸው ሌብነትና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የቀረበው ረቂቅ ፓሊሲ ላይ ባለድርሻ አካላት ለሰጡት ሀሳብና አስተያየት ምስጋና አቅርበው፣ የትውልድ ሥነምግባር ግንባታ ላይ እያንዳንዱ ዜጋ የሚጠበቅበትን ድርሻ ሊወጣ ይገባል ብለዋል:: በውይይቱ ላይ የፓሊሲው ዋና ዋና ጉዳዮች በሰባት መሠረታዊ ነጥቦች የተቀመጡ ሲሆን፣ የሥነምግባር መርሆዎች፣ የህፃናትን ሥነምግባር በማነፅ የቤተሰብ ሚና፣ የወጣቶች ሥነምግባር፣ የተቋማት የሥነምግባር ግንባታ ስራዎች፣ የተቋማት የውስጥ መከላከል አሰራር ስርዓት፣ የሙስና ወንጀል ህግ አተገባበር እንዲሁም የተመዘበረ ሀብት የማስመለስና ማስተዳደር በሚሉ ሀሳቦች ላይ ውይይቱ አተኩሯል::

የውይይቱ ተሳታፊዎች በበኩላቸው ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የተለያዩ ዘርፎች ፓሊሲው በደንብ ቢያያቸው፣ የሚባክኑ የመንግስት ሀብቶችን የሚቆጣጠርበት ጥብቅ መመሪያ ቢዘጋጅ፣ ረቂቅ ፖሊሲው ላይ ህዝቡ በስፋት ውይይት ቢያደርግ የሚሉና ሌሎችም አስተያየቶች ቀርበው በመድረኩ ላይ ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል:: ጠንካራ የፀረ-ሙስና እርምጃ ተግባራዊ ለማድረግ ያለመ ሀገር አቀፍ ረቂቅ ፓሊሲ ላይ ከወጣቶች ጋር ውይይት ተደረገ

በተመሳሳይ መረጃ የአዲስ አበባ ከተማ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከከተማው ወጣቶችና ስፓርት ቢሮ ጋር በመተባበር የፀረ-ሙስና እርምጃ ተግባራዊ ለማድረግ ባለመው ሀገር አቀፍ ረቂቅ ፓሊሲ ላይ ከወጣቶች ጋር ወይይት አድርጓል::

# የተመዘበረ ሀብት ለማስለመስ ዓለም አቀፍ ትብብር እና ቅንጅት እንደሚያስፈልግ ተገለፀ



ሙስናን ጨምሮ በተለያየ ምክንያት ተመዝብሮ ወደ ውጭ የሚሸሽ ሀብት ለማስመለስ የሚደረገውን ጥረት የሚደገፍ እና በየአህጉራቱ የተካሄዱትን እንቅስቃሴ የሚገመገም 10ኛው ዓለም አቀፍ የተመዘበረ ሀብት ማስመለስ ኔትወርኮች የግምገማ መድረክ ከሰኔ 12-13/2016 ዓ.ም ድረስ በኔዘርላንድ ዘሄግ ከተማ ተካሄዷል:: በአውሮፓ ህብረት ዋና የፓሊስ መስሪያቤት (Europol) በተዘጋጀው መድረክ በየአህጉሩ የተደራጁ ኔትዎርኮች በ2016 ዓ.ም ያከናወኗቸውን ስራዎች አፈፃፀም ያቀረቡ ሲሆን፥ በተለይም ቀልጣፋና የተቀናጀ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት በሀገር ውስጥ ተቋማት፣ በሀገራት እና ዓለም አቀፍ ደረጃ ሊኖር ስለሚገባ ቅንጅትና ትብብር በሚመለከት በስፋት ውይይት ተደርጎበታል::

እንዲሁም የተመዘበረ ሀብት ለማስመለስ የሚደረጉ ጥረቶች ለማጠናከር የዓቅም ግንባታ እና የልምድ ልውውጥ ስራዎች በስፋት እንዲከናወኑና በየአህጉሩ የተደራጁ ኔትዎርኮች አባል ያልሆኑ አገራት አባል እንዲሆኑ ትኩረት ተሰጥቶበት እንዲሰራ ስምምነት ላይ ተደርሷል:: በመድረኩ የምስራቅ አፍሪካ የተመዘበረ ሀብት ማስመለስ ኔትወርክ (ARINEA) በመወከል የኔትወርኩ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ሀረጎት አብረሃ የተሳተፉ ሲሆን፥ የኔትወርኩ አፈፃፀም ለጉባኤው አቅርበው ውይይት ተደርጎበታል::

ከመድረኩ ጎን ለጎን የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥልጠና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሀረጎት አብርሃ ሄግ ከተማ ከሚገኘው የስልጠና አካዳሚ ጋር በጋራ ለመስራት በሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ ውይይት አካሄደዋል:: በውይይቱም በሥነምግባር ግንባታ፣ በሙስና መከላከል እና በመልካም አስተዳደር ዙሪያ የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠት ከፍተኛ ልምድ እና እውቅና ካላው ዓለም አቀፍ የስልጠና አካዳሚ (The Hague Academy for Local Governance) ጋር በቀጣይ በጋራ ለመስራት በሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ ከአካዳሚው የዓቅም ግንባታ



ፕሮግራም ኃላፊ ጋር ውይይት ተደርጓል::የመስራቅ አፍሪካ የተመዘበረ ሀብት ማስመለስ ኔትወርክ ጠቅላላ ጉባኤ በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አስተናጋጅነት በሀገራችን መዲና አዲስ አበባ በቅርቡ መካሄዱ ይታወቃል::



ከሙስና የፀዳች ኢትዮጵያ!

# በክልሉ ለሚገኙ የተቋም የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊዎች በሀብት ማሳወቅና ምዝገባ አስፈላጊነት ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጠ

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በክልሉ ለሚገኙ ለፍትህ ተቋማትና ለባለድርሻ ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ዳይሬክተሮችና ቡድን መሪዎች በሀብት ማሳወቅና ምዝገባ አስፈላጊነት ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በመድረኩ የተገኙት የኮንሶ ዞን ዋና አስተዳዳሪ የተከበሩ ኢንጂነር ፍሬዘር ኮርባይዶ እንደገለፁት በብዙ ጥረት የሚገኘውን የህዝብና የመንግስት ሀብት ከሙስና እና ብልሹ አሰራር ካልታደግን ከመልካም አስተዳደር እጦት ችግር ባለፈ ለመንግሥትም ቢሆን አደጋን ይፈጥራል ብለዋል፡፡





ይህ እንዳይሆን ከሚያግዙ ተግባራት አንዱ ሀብት ማሳወቅና ማስመዝገብ መሆኑን ጠቁመው፥ ለዚህም በዞኑ የሚገኙ ሁሉም አመራሮች ሀብታቸውን እንዲያሳውቁና እንዲያስመዘግቡ በሚደረገው ጥረት አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ እንደሚያደርጉም ቃል ገብተዋል፡፡ የክልሉ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሶፎኒያስ ደስታ በበኩላቸው ሙስና ከወንጀሎች ሁሉ የከፋ ወንጀል በመሆኑ የሀገሪቱን ልማትና ዕድገት የሚገታ ክፉ ነቀርሳ ነው፡፡ ለዚህም ለህብረተሰቡ ግንዛቤ እየፈጠርንና በፀረ-ሙስና ትግሉ ንቁ ተሳፎ እንዲያደርግ አስፈለጊውን ሁሉ እያደረግን እንገኛለን ብለዋል፡፡ ኮሚሽነሩ አክለውም ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከልና ህብረተሰቡ የሚፈልገውን መልካም አስተዳደር ለማስፈን በሚደረገው ብርቱ ጥረት የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራ አውንታዊ አስተዋፅኦው የጎላ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በክልሉ የሚገኙ ከስድስት ሺህ በላይ አመራሮችን ሀብት ምዝገባ የተጀመረ መሆኑን ገልፀው፥ የፍትህ ተቋማትና ባለድርሻ አካለት የጋራ ተሳትፎ ተጠናክሮ መሄድ እንዳለበት በመታመኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናው ማስፈለጉን ተናግረዋል፡፡ ተሳታፊዎችም የበኩላቸውን እንዲወጡ አሳስበዋል፡፡ከተሳታፊዎቹ በርከት ያሉ ሀሳብ፣ አስተያየትና ጥያቄዎች የተነሱ ሲሆን፥ በኮሚሽኑ አመራሮች ሰፋ ያለ ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ በኮንሶ ዞን ካራት ከተማ በተካሄደው የስልጠና መድረክ የክልሉ ዋና ኦዲት ቢሮ ኃላፊ የተከበሩ አቶ አበባየሁ ኤርሚያስ፣ የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ ምክትል ኃላፊ ወ/ሮ አዜብ ዘውዱን ጨምሮ የተለያዩ ቢሮ ኃላፊዎችና ተወካዮች ተገኝተዋል፡፡

# የኮሚሽኑ ካውንስል በ11 ወራት የሥራ እንቅስቃሴ እና በ2017 በጀት ዓመት የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ ውይይት አካሄደ





የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ካውንስል ጉባኤ በ2016 በጀት ዓመት የሥነምግባር ግንባታና የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ በ11 ወራት ያለበትን ሁኔታ እና በ2017 በጀት ዓመት በልዩ ትኩረት የሚካሄዱ የኮሚሽኑ የሪፎርም ሥራዎችን ለመለየት ያለመ ውይይት አካሂዷል፡፡ ካውንስሉ በቀጣይ በጀት ዓመት ሰፋፊ የሪፎርም ሥራዎችን ለማከናወን አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡



# በኦሮሚያ ክልል የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች የሙስና መከላከል ጥረቱን እንዲያግዙ ተጠየቀ

በኦሮሚያ ክልል የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች ትውልዱ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን እንዲፀየፍ የሚያደርጉ ሙያዊ ስራዎችን በመስራት የሙስና መከላከል ጥረቱን እንዲያግዙ የክልሉ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጠየቀ፡፡ ኮሚሽኑ በሙስና መከላከልና በሥነምግባር ግንባታ ዙሪያ የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ እንዲችሉ የምክክር መድረክ በአዳማ አባገዳ አዳራሽ አካሂዷል፡፡





የኮሚሽኑ ኮሚሽነር አቶ አብደላ ኦገቴ በተለይ ለኢዜአ እንደገለጹት በትውልድ ሥነምግባር ግንባታ ሂደት ውስጥ የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች ሚና ወሳኝ ነው፡፡ መድረኩም አዲሱ ትውልድ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን እንዲፀየፍ ብሎም ሀገርን ከሙስና፣ ከብልሹ አሰራርና ምዝበራ ለመጠበቅ የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች በሙያቸው እንዲያግዙ መዘጋጀቱን አስረድተዋል፡፡ በዚህም ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመዋጋት በሚደረገው ጥረት ውስጥ በፊልም፣ በድራማና በሌሎች የኪነ-ጥበብ ስራዎች ትውልዱ የሙስና እና ብልሹ አሰራርን አስከፊነትና በሀገርና ህብረተሰብ ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ለማስገንዘብ እንዲሰሩም ጠይቀዋል፡፡

የኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር ወ/ሮ አባይነሽ ተፈራ በበኩላቸው ኮሚሽኑ በአስቸኳይ የሙስና መከላከል ሥራ ከ470 ሚሊዮን ብር በላይ ጥሬ ገንዘብ ከምዝበራ መታደጉን ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም በሙስና የተመዘበረ ከ149 ሺህ ካሬ ሜትር የከተማና 1 ሺህ 632 ሄክታር የገጠር መሬት ማስመለስ መቻሉን ተናግረዋል፡፡

በተጨማሪም 17 ተሽከርካሪዎች፣ 274 ላፕቶፕና ዴስክ ቶፕ ኮምፒዩተሮችን ጨምሮ ሌሎች ቋሚና ተንቀሳቃሽ የሕዝብና የመንግሥት ንብረት ማስመለሱን ወ/ሮ አባይነሽ አስታውቀዋል፡፡

ኮሚሽኑ በተለይም በጨረታ፣ በፕሮጀክቶች ግንባታ፣ በግዥ፣ በቅጥርና ዝውውር፣ በመንግሥት መመሪያዎች ተፈፃሚነትና የአሰራር ጉድለቶች ላይ 22 አስቸኳይ የሙስና መከላከል ጥናቶችን በማካሄድ የሙስና ተጋላጭነትንና ምዝበራን ማስቀረቱን ገልጸዋል፡፡

# ሀሰተኛ ሰነድ በማዘጋጀትና በማሰራጨት የተጠረጠረው ግለሰብ ከነ-ኤግዚቢቱ በቁጥጥር ሥር ማዋሉን የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ገለፀ



ሀሰተኛ ሰነድ በማዘጋጀትና በማሰራጨት የተጠረጠረው ግለሰብ ከነ-ኤግዚቢቱ በቁጥጥር ሥር ማዋሉን የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ገልጿል፡፡ ተጠርጣሪው ሊያዝ የቻለው በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 ልዩ ቦታው ዳንኤል ሆቴል ፊት ለፊት ከረሜላ ህንፃ አንደኛ ፎቅ ሁለት ሱቆች በኢንተርኔት ቤት ሽፋን በሀገር ላይ ጉዳት ለማድረስ ሆንብሎ የተለያዩ ሀሰተኛ ፓስፖርቶች፣ የጤና ምርመራ ውጤቶች፣ COC እና ሌሎች ሀሰተኛ ሠነዶችን አዘጋጅቶ ለኅብረተሰቡ ለማሰራጨት ሲል የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ማዕከላዊ ወንጀል ኢንተለጀንስ ዋና መምሪያ ከኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ጠቅላይ መምሪያ ጋር በመቀናጀት ባደረጉት ጥናትና ክትትል ከነ-ኤግዚቢቱ በቁጥጥር ሥር ሊውል ችሏል፡፡

በተጨማሪም ፖሊስ ሰኔ 27 ቀን 2016 ዓ.ም ከፍርድ ቤት የብርበራ ፍቃድ በማውጣት በተጠርጣሪው መኖርያ ቤት ባደረገው ብርበራ በዝግጅት ሂደት ላይ ያሉ ሀሰተኛ የቀበሌ መታወቂያዎችን፣ የፌደራልና ክልል የልደት የምስክር ወረቀቶችን፣ የአየር መንገድ በረራ ትኬቶችን፣ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የባለሙያዎች የምስክር ወረቀቶችን፣ የአዲስ አበባ ከተማ ገቢዎች ባለስልጣን ግብር ከፋይ ሰርትፍኬቶችን፣ የእጅ በእጅ ደረሰኞችን፣ የትምህርት ማስረጃዎችንና በርካታ ክብ ማህተሞችን መያዝ መቻሉን የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ አስታውቋል፡፡

ተጠርጣሪው ሀሰተኛ ሰነዶቹን ለማዘጋጀት ይጠቀምባቸው የነበሩ በርካታ ሃርድ ዲስኮች፣ ሁለት ላፕቶፖች፣ ሲዲዎች፣ ፍላሾች እና የተለያዩ ሀሰተኛ ሰነዶችን ለማተም የሚያገለግሉ ጠንካራ ወረቀቶችን በኢግዚቢት መያዛቸውን ፖሊስ ጨምሮ ገልጿል፡፡ ሀሰተኛ ሰነድ በማዘጋጀት ከተጠረጠሩት ግለሰቦች መካከል አንድ ተጠርጣሪ በፖሊስ ቁጥጥር ሥር የዋለ ሲሆን፣ ሌሎች ተጠርጣሪዎችን ለመያዝ ፖሊስ ክትትሉን አጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ በመሆኑም ኅብረተሰቡ ተመሳሳይ የወንጀል ድርጊቶችን በመፀየፍ በተመሳሳይ ወንጀል ላይ የተሰማሩ ግለሰቦችና ቡድኖችን አሳልፎ ለፀጥታ አካላት በመስጠት አስፈላጊ ትብብር እንዲያደርግና ተቋሙ ባዘጋጀው የዜጎች ተሳትፎ መተግበሪያ (EFPApp) በመጠቀም ወይም በ991 ነፃ የስልክ መስመር በመደወልና መልዕክት በመላክ ጥቆማ እንዲሰጥ የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ጥሪውን ያቀርባል፡፡



# ለሆቴል ግንባታ በሚል በሀሰተኛ ሰነድ ፌሮ ብረቶችን ከቀረጥ ነጻ ከውጭ አስገብቶ ለግል ጥቅም ያዋለው ግለሰብ በስድስት ዓመት ጽኑ እስራት ተቀጣ



የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ችሎት በዋለው ችሎት በኦሮሚያ ክልል ሸገር ከተማ ቡራዩ ክ/ከተማ ነዋሪ የሆነው ዮሴፍ ዳዊት ሖማ በተባለ ተከሳሽ ላይ የቀረበበት የሙስና ወንጀል ክስና የግራ ቀኝ ማስረጃዎችን መርምሮ የጽኑ እስራት እና የገንዘብ መቀጮ ውሳኔ አስተላልፏል:: የፍትህ ሚኒስቴር የሙስና ወንጀሎች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ ተከሳሹ በ2008 ዓ.ም የወጣውን የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር- 980/2008 በአንቀፅ-49 ንዑስ ቁጥር 3 ስር የተደነገገውን ድንጋጌ እና በ2007 ዓ.ም የወጣውን የሙስና አዋጅ ቁጥር 881/2007 በአንቀፅ 23 ንዑስ ቁጥር 1 (ሀ) እንዲሁም ንዑስ ቁጥር 2 እና 3 ስር የተደነገገውን ድንጋጌ በመተላለፍ ከ10 ወራት በፊት ክስ ቀርቦበት ነበር::

ክሱም ተከሳሹ ከሌሎች ግብረአበሮቹ ጋር በመሆን ለሆቴል ግንባታ በሚል ምክንያት በሀሰተኛ ሰነድ 40 ሚሊየን ብር በላይ የሚገመት የፌሮ ብረቶችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ምንም አይነት የግንባታ ስራ ሳያከናውን ለግል ጥቅሙ አውሎታል የሚል ነበር:: ሀሰተኛ መረጃዎችን በማቅረብ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ለማውጣት መስከረም 19 ቀን 2015 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ዋይኤ ሆቴል ኤንድ ሪዞርት ኃላ/የተ/የግ/ማህበር በሚል ስያሜ በውጪና በሀገር ውስጥ ባለሃብት ቅንጅት ለማቋቋም እና እርሱም ድርጅቱን በስራ አስኪያጅነት ለመምራት የኢትዮጵያ አንቨስትመንት ኮሚሽን በመስከረም 30 ቀን 2015 ዓ.ም ከአዋሽ ባንክ በተጠቀሰ ሂሳብ ቁጥር ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የተጻፈና በዋይኤ ሆቴል ኤንድ ሪዞርት ኃላ/የተ/የግ/ ማህበር ስም ሂሳብ ተከፍቶ 7 ሚሊየን 890 ሺህ ብር ገቢ የተደረገ መሆኑን የሚገልፅ የባንክ ሰነድ ማቅረቡን ጠቅሶ በክሱ ላይ ዐቃቤ ሕግ አስፍሯል::

ነገር ግን ተከሳሹ የንግድ ምዝገባውን በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ለማከናወን ከአዋሽ ባንክ ያቀረባቸው የአቅም ማሳያ የባንክ ሰነዶች ከባንኩ ያልተሰጡና ሀሰተኛ ማስረጃዎች መሆናቸው የተረጋገጠ በመሆኑ፤ በፈፀመው ሀሰተኛ የንግድ ምዝገባ ማስረጃዎችን በማቅረብ በንግድ ምዝገባ መመዝገብ ወንጀል ክስ ቀርቦበታል:: በተለይም በቀረበበት በሁለተኛ ክስ ላይ እንደተጠቀሰው ሀሰተኛ የባንክ ማስረጃዎች በማቅረብ ዋይኤ ሆቴል ኤንድ ሪዞርት ኃላ/የተ/የግ/ማህበር የሚባል የንግድ ድርጅት ካስመዘገበ እና የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከወጣ በኋላ በድርጅቱ ስም ባለ ኮኮብ ደረጃ ሆቴል ለማስገንባት ቅድመ ሁኔታዎችን እንደጨረሰና ለግንባታውም 8 ሺህ 500 ቶን ፌሮ ብረት እንደሚያስፈልገው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የአገልግሎት ፕሮጀክቶች ማበረታቻ ክፍልን መጠየቁ በክሱ ዝርዝር ሰፍሯል::

ብረቱ ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲገባ እንዲፈቀድለት ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቂርቆስ ክ/ከተማ ጽ/ቤት በይዞታ መለያ ቁጥር እና የሴሪ ቁጥር የተጠቀሰበት በመጋቢት 12 ቀን 2015 ዓ.ም ለዋይኤ ሆቴል ኤንድ ሪዞርት ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ለተባለ ድርጅት እንደተሰጠ የሚገልፅ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና ከአዲስ አበባ ከተማ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን በጥቅምት 15 ቀን 2015 ዓ.ም በዋይኤ ሆቴል ኤንድ ሪዞርት ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ለተባለ ድርጅት ለሆቴል አገልግሎት ባለ 12 ወለል ሕንጻ ለመገንባት የግንባታ ፈቃድ ምስክር ወረቀት እንደተሰጠው የሚገልፅ ሰነድ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶችን በማያያዝ በታህሳስ ወር 2015 ዓ.ም ማመልከቱ ተጠቅሷል::

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ለሆቴሉ ግንባታ ያስፈልጋል በማለት ተከሳሹ ካቀረበው የብረት መጠን ውስጥ በመጀመሪያ ዙር 1 ሺህ 500 ቶን ባጠቃላይ 40 ሚሊየን 665 ሺህ 842 ብር ከ41 ሳንቲም ቀረጥና ታክስ ሊያስከፍል የሚችል ፌሮ ብረት ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲያስገባ እንዲፈቀድለት ለገንዘብ ሚኒስቴር በጻፈው ደብዳቤ መሰረት ተከሳሹ 256 ጥቅል ብረት በድሬዳዋ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባ ሲሆን፣ ነገር ግን ተከሳሽ የተጠቀሰውን ፌሮ ብረት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት እንዲፈቀድለት ያቀረባቸው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እና የግንባታ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ሀሰተኛ መሆናቸው መረጋገጡን ዐቃቤ ሕግ በክሱ ላይ ዘርዝሯል::

በመሆኑም ተከሳሹ በፈፀመው መንግስታዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት ወይም በሀሰተኛ ሰነድ መገልገል ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ ተመስርቶበታል:: ተከሳሹ በወቅቱ በተረኛ ችሎት ቀርቦ ክሱ እንዲደርሰው ከተደረገ በኋላ የተከሰሰበት ድንጋጌ ዋስትና የሚያስከለክል ድንጋጌ መሆኑ ተጠቅሶ በማረሚያ ቤት ሆኖ ጉዳዩን እንዲከታተል ታዞ የነበረ ሲሆን የተከሰሰበት የወንጀል ድርጊትን አለመፈፀሙን ጠቅሶ የሰጠውን የዕምነት ክህደት ቃል ተከትሎ ዐቃቤ ሕግ የሰነድና የሰው ምስክር አቅርቦ አሰምቷል::

ፍርድ ቤቱም የዐቃቤ ሕግ ማስረጃን መርምሮ በተከሰሰበት አንደኛው ክስ ከሁለተኛ ክስ ጋር ተጠቃሎ በአንቀጽ 23 ንዑስ ቁጥር 1 ሀ እና ንዑስ ቁጥር 2 እና 3 ስር እንዲከላከል ብይን የሰጠ ቢሆንም ተከሳሹ በተገቢው መከላከል አለመቻሉ ተገልጾ የጥፋተኝነት ፍርድ ተላልፎበታል:: ከዚህም በኋላ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኝ የቅጣት አስተያየት መርምሮ በመካከለኛ ደረጃ የተከሳሹን 5 የቅጣት ማቅለያ አስተያየቶችን በመያዝ በ6 ዓመት ጽኑ እስራትና በ1 ሺህ 500 ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ተወስኗል::

# ኮሚሽኑ ከክልልና ከተማ አስተዳደር ኮሚሽነሮች ጋር የቨርቿል ውይይት አካሄደ



የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በ2016 በጀት ዓመት የሙስና መከላከል ጥናት ተግባራት ዙሪያ ከክልልና ከከተማ አስተዳደር የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽነሮች የሥራ ኃላፊዎች ጋር የቨርቿል ውይይት አካሄዷል:: በውይይቱ የሙስና መከላከል ጥናት፣ የአስቼኳይ ሙስና መከላከል፣ የሙስና መረጃ አስተዳደር እንዲሁም የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ እንዲሁም የሀብት ምዝገባ ትክክለኛነት ማጣራት ጉዳዮች ተዳሰዋል:: በቀጣይ በጀት ዓመት የድጋፍና ክትትል ስራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል በውይይቱ ወቅት ተጠቁሟል:: በተያያዘ መረጃ ኮሚሽኑ ለክልልና ከተማ አስተዳደር ሥልጠና ባለሙያዎች በበይነ መረብ የታገዘ የአሰልጣኞች ስልጠና /TOT/ ሰጥቷል::

# ለፕላንና ልማት ዘርፍ አመራሮች በሥነምግባራዊ አመራርነት ላይ ስልጠና ተሰጠ



የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር እና ለተጠሪ ተቋማት አመራሮች በሥነምግባራዊ አመራርነት ላይ ስልጠና ሰጥቷል፡፡ በስልጠናው የተገኙት የፕላንና ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ክብርት ወ/ሮ ጥሩማር አባተ እንደገለፁት አንዱ የፀረ-ሙስና ትግልን የተሻለ የሚያደርገው የአቅም ግንባታ ስልጠና መሆኑን ተናግረው፥ በተለይ የመካከለኛ አመራሩን በተመረጡ ርዕሶች ላይ የተሻለ ስልጠና በመስጠት በየጊዜው አሰራሮችን ለመመርመር እና በተቋሙ የሥነምግባር ዕሴቶች እንዲጠበቁ እንዲሁም ከሙስና የፀዳ አሰራርን ለመከተል ስልጠናው አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

ሚኒስትር ዴኤታዋ አይይዘውም ሙስና የምናደርገውን የመልማት ትግል፣ ፈጣን ዕድገት ለማምጣትና ማህበረሰባችን የተሻለ የኑሮ ሁኔታ እንዲፈጠር ለማድረግ የምናደርገውን ሁለተናዊ ዕድገት የሚገታ መሆኑን ተረድተን ካልታገልነው ሀገርን እና ትውልድን የሚያጠፋ አሳሳቢ ጉዳይ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ስለሆነም ይሄንን ችግር ለማስተካከልና የተሻለ ለማድረግ አመራሩ





ቁርጠኛና ሥነምግባርን የተላበሰ እንዲሆን ከሚያደርጉ ሁኔታዎች አንዱ ስልጠና መስጠት አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ስልጠናው በኮሚሽኑ የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ስልጠና ዴስክ ኃላፊ በሆኑት በአቶ ኪዳነ ምህረት እና በአቶ አንተነህ ኃይሌ የተሰጠ ሲሆን፣ በሥነምግባራዊ አመራርነት ምንነት፣ አስፈላጊነት፣ የሥነምግባራዊ አመራርነት ክህሎቶችና መርሆዎች እንዲሁም የሥነምግባራዊ አመራርነት መሠረታዊ መገለጫ ባህሪያት እና ሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እንዲሁም ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አኳያ የዘርፉ አመራር ሚና በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ነው፡፡

# ሀሰተኛ የቅጣት ማቅለያ አቅርበው ቅጣት እንዲቀልላቸው ያስደረጉ ተከሳሾች በጽኑ እስራት ተቀጡ



የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት አሳሳችና ሀሰተኛ የቅጣት ማቅለያ ማስረጃ በማቅረብ ቅጣት እንዲቀልላቸው አስደርገዋል ያላቸውን ሶስት ተከሳሾች በጽኑ እስራትና በገንዘብ እንዲቀጡ ወሰነ፡፡ በረከት ብርሃኑ ሞሲሳ፣ ዮናስ ካሳ በጋሻው እና ዳግም ውብሸት ወንድማገኝ የተባሉት ተከሳሾች፥ በሌላ ችሎት አቅርበውት የነበረው ሕዝባዊና መንግሥታዊ የቅጣት ማቅለያ ሰነዶች ሀሰተኛ መሆናቸውን በማጣራት የሙስና ወንጀልን ለመከላከል በወጣው አዋጅ ሥር የተመላከተውን ድንጋጌ ተላልፈዋል በሚል የፍትሕ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ ክስ መስርቶባቸው ነበር፡፡

ከሁለት ዓመት በፊት በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ የሰው ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎት በከባድ ውንብድና ተግባር በተከሰሱበት የወንጀል ተግባር የግራ ቀኝ ማስረጃ ተጣርቶ የዐቃቤ ሕግን ማስረጃ ባለመከላከላቸው የጥፋተኝነት ፍርድ ተላልፎባቸዋል፡፡ ይሁንና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 82 እና 86 መሠረት የሚጣልባቸው ቅጣት እንዲቀልላቸው ለቅጣት ማቅለያነት የሚውሉ ሀሰተኛ መንግስታዊና ሕዝባዊ የሰነድ ማስረጃዎችን ማቅረባቸው ተጠቅሷል፡፡

1ኛ ተከሳሽ ከሁለት ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች ድጋፍ ማድረጉን፣ በኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኀበር ደም መለገሱን፣ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 የማኀበረሰብ ዓቀፍ ፖሊስ እና ለአረንጓዴ ዐሻራ ድጋፍ ማድረጉን እንዲሁም ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ቦንድ መግዛቱን የሚገልጹ ሀሰተኛ የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቧል ተብሏል፡፡

2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾችም በየደረጃው ሕዝባዊና መንግሥታዊ የሆኑ ለቅጣት ማቅለያነት የሚያገለግሉ ሀሰተኛ ሠነዶችን በማቅረብ ሀምሌ 14 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት ቅጣቱ ቀሎ እንዲወሰን ያደረጉ መሆኑን ጠቅሶ ዐቃቤ ሕግ ጠቅሶ ክስ አቅርቧል፡፡

የቀረበውን ሀሰተኛ የቅጣት ማቅለያ ማስረጃ ሠነዶችን ማቅረብ ክስና የግራ ቀኝ ክርክር የመረመረው 2ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ተከሳሾቹ ወንጀሉን መፈፀማቸውን በማረጋገጥ ጥፋተኛ ተብሏል፡፡ በዚሁ መሠረትም 1ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች እያንዳንዳቸው በ3 ዓመት ጽኑ እስራት እና በ500 ብር የገንዘብ ቅጣት እንዲሁም 2ኛ ተከሳሽ በ2 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እስራትና በ500 መቶ ብር የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጡ ተወስኗል፡፡

# የኮሚሽኑ አመራሮችና ሠራተኞች በሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ረቂቅ ፖሊሲ ላይ ውይይት አካሄዱ





የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራሮችና ሠራተኞች በሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ረቂቅ ፖሊሲ ላይ ውይይት አካሄደዋል፡፡ የውይይቱ ዓላማ በሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ረቂቅ ፖሊሲ ላይ የኮሚሽኑ አመራሮችና ሠራተኞች ውይይት በማድረግ ተጨማሪ ግብዓት ለማሰባሰብ ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ በመድረኩም ረቂቅ ፖሊሲው የቀረበ ሲሆን፥ የውይይቱ ተሳታፊዎችም ለረቂቅ ፖሊሲው ግብዓት የሚሆን ሀሳብና አስተያየት በመስጠት ከመድረኩ ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶበት የጋራ ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡

## ኤጀንሲው በ11 ወራት 24 አመራሮችንና 74 ባለሙያዎችን ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረጉን ገለፀ



የአዲስ አበባ ከተማ ሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ የ2016 በጀት ዓመቱን የስራ አፈጻጸምና አገልግሎት አሰጣጥን ከሁሉም ክፍለ ከተሞች የተወጣጡ የማህበረሰብ ተወካዮች ጋር ውይይት አካሄዷል፡፡ የኤጀንሲውን አገልግሎት አሰጣጥ ዘመናዊና ተደራሽ ለማድረግ ከስያሜው ጀምሮ አሰራሩን በማሻሻል ሪፎርም አድርጎ ወደ ስራ መግባቱን የአዲስ አበባ ሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ዮናስ አለማየሁ ገልፀዋል፡፡

አቶ ዮናስ አክለውም በተቋሙ በስፋት ይስተዋል የነበረውን ብልሹ አሰራር በመቀየር ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን አብራርተው፥ በዚህም የክትትልና ቁጥጥር ስራን በማጠናከር በ11 ወራት 24 አመራሮችና 74 ባለሙያዎች ተጠያቂ እንዲሆኑ መደረጉን ገልፀዋል፡፡ የውይይቱ ተሳታፊዎች በበኩላቸው በተቋሙ የተከናወነው ሪፎርም ቀደም ሲል ይስተዋሉ የነበሩ ችግሮችን በመሰረታዊነት የፈታ መሆኑን ተናግረው፥ የአገልግሎት አሰጣጡን ፈጣን፣ ግልጽና ተጠያቂነት ያለበት በማድረግ ሂደት የተጀመሩ ስራዎች ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል ብለዋል፡፡



## "በመልካም ሥነምግባር የታነፀ፣ ሀገር ተረካቢ ዜጋ ለማፍራት የበኩላችንን ድርሻ እንወጣ!" በሚል መሪ ሀሳብ ስልጠና ተሰጠ

የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና መከታተል ቡድን "በመልካም ሥነምግባር የታነፀ፣ ሀገር ተረካቢ ዜጋ ለማፍራት የበኩላችንን ድርሻ እንወጣ!" በሚል መሪ ቃል በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ ገላን ልዩ የወንዶች አዳሪ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ንቅናቄ አካሄደ፡፡ የክፍለ ከተማው የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና መከታተያ ቡድን መሪ አቶ ደሴ አባተ በት/ቤቱ ተገኝተው ሙስናን የሚፀየፍ፣ በመልካም ሥነምግባር የታነፀ፣ ሀገር ተረካቢ ዜጋ መፍጠር ላይ የትምህርት ተቋማት ሚና ከፍተኛ መሆኑን መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡ ተማሪዎች በት/ቤታቸው የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ክበብ በማቋቋም መልካም ሥነምግባር የተላበሰ እና ለሌሎች አርዓያ በመሆን የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ፅንሰ ሀሳቡንና አላማን ከግብ ማድረስ እንደሚጠበቅባቸው ተገልጿል፡፡



በተያያዘም በሥነምግባር የታነፁ፣ መምህራንና ወላጅ የሚካብር፣ የማህበረሰቡን ጠቃሚ እሴት ጠብቆ የሚያስቀጥል፣ ብልሹ አሰራንና ሌብነትን የሚፀየፍ ትውልድ ለማፍራት በትምህርት ቤት ማህበረሰብ ላይ ግንዛቤ ለመፍጠር አላማ ያደረገ ንቅናቄ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች በራሳቸው የሚተማመኑ፣ ኩረጃን የሚፀየፍና በትምህርታቸው የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚጠበቅባቸው መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡



## ፀረ-ሙስና

በፌደራል
የሥነምግባር እና
የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
የሚዘጋጅ ወርሃዊ
ጋዜጣ

| | |
|---|---|
| ስልክ | 011552-77-79 |
| ፖ.ሳ.ቁ | 34799 |
| ኢ-ሜይል | FeaccEthiopia2013@et |
| ድረ-ገጽ | www.feacc.gov.et |
| ፌስቡክ | www.facebook.com/feaccOfficial |
| ቴሌግራም | t.me/feacc |
| ትዊተር | www.twitter.com/EthiopiaFeacc |
| ዩቲዩብ | Federal Ethics & Anti-Corruption Commission |

ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች
www.feaccdars.gov.et

ለፌደራል የሥነምግባር
እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
የሙስና ወንጀል ጥቆማ
መስጫ አድራሻዎች

| | |
|---|---|
| ስልክ | 011552 77-92/ 011553-38-52 |
| ሞባይል | 0935947533 |
| ፖ.ሳ.ቁ | 34799 |
| ድረ-ገጽ | www.feacc.gov.et |
| ኢ-ሜይል | CorruptionReportEthiopia@feacc. gov.et |
| ቴሌግራም | t.me/CorruptionPointing |
| ዋትስአፕ | wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1 |


# ርዕሰ-አንቀፅ

## ሙስና ልማትን የሚያደናቅፍ ድንበር ተሻጋሪ ወንጀል ነው!

ሙስና የአገርን ማህበራዊ፣ ፖሊቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት የሚገታ፣ ዜጎችን ለከፋ ድህነት የሚዳርግ፣ ገንዘብን ከአገር የሚያሸሽ ድንበር ተሻጋሪ ወንጀል ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ልማት ላይ ሊውሉ የሚችሉ በርካታ የህዝብና የመንግስት ሀብቶች የሙስና ሰለባ ሲሆኑ ይስተዋላል፡፡ ይህ ድርጊት የሚያደርሰው ጉዳት ከአገር አገር ይለያይ እንጂ በመላው አለማችን ተዳርሶ እንደሚገኝ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ ለአብነት ያህል እንደ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ፎረም መረጃ በየዓመቱ በጉቦና ስርቆት ብቻ የሚፈጸም ሙስና ከ3 ነጥብ 6 ትሪልዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ የአለማችን ኢኮኖሚ ላይ ጉዳት እንደሚያደርስ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

ሙስና ለሰው ልጆች ሰላም ማጣት፣ ለፍትህ መጓደል፣ ለሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ ለስደት፣ ለተፈጥሮ ሀብት ብክነትና ለአከባቢ ብክለት የሚዳርግ ዓለም አቀፋዊ ችግር ነው፡፡ በዚህ ችግር ክፉኛ ከተጠቁ ክፍለ ዓለማት ውስጥ አፍሪካ ግንባር ቀደም ስትሆን፣ ሀገራችን ኢትዮጵያም የዚህ አደገኛ ችግር ሰለባ ከሆኑት ሀገራት ውስጥ ትጠቀሳለች፡፡ ይህንን ዓለም አቀፋዊ ችግር ለመከላከል አገሮች በተናጠል ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ በተጨማሪ በጋራ ሊታገሉት የሚያስችላቸው ዓለም አቀፍ ስምምነት (ኮንቬንሽን) እንዲኖር በተባበሩት መንግስታት ድርጅት በኩል ጥረት ተደርጓል፡፡

በተደረገው ጥረትም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እ.ኤ.አ ከዲሴምበር/ታህሳስ 4/2000 ጀምሮ ስምምነቱን በማርቀቅ የተለያዩ ዝግጅቶችን አድርጓል፡፡ የረቂቅ ስምምነቱ እ.ኤ.አ ኖቬምበር/ከህዳር 9-12/2003 በሜክሲኮ “ሜሪዳ” በተካሄደው የድርጅቱ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ለአባል አገሮች ቀርበው በውሳኔ ቁጥር 58/422 ዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ኮንቬሽን ሆኖ ሊፀድቅ ችሏል፡፡

ስምምነቱ ለፀረ-ሙስና ትግሉ ያለውን ፋይዳ ለማስገንዘብና በሙስና አስከፊነት ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር እ.ኤ.አ ዲሴምበር 9/ በኢትዮጵያ አቆጣጠር ህዳር 30/ ዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን ሆኖ በየዓመቱ እንዲከበርም በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ተወስኗል፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ዕለቱ ስምምነቱን በፈረሙ አገሮች ዘንድ በየዓመቱ የስምምነቱን ጠቀሜታ በማስገንዘብና ሌሎች እንደየ አገሮች ተጨባጭ ሁኔታ በፀረ-ሙስና ትግሉ ዙሪያ ለህብረተሰቡ ግንዛቤ በሚፈጥሩ ዝግጅቶች እየተከበረ ይገኛል፡

ኢትዮጵያ ስምምነቱን በማርቀቅ ሂደትም ሆነ ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በማቅረብ እ.ኤ.አ ዲሴምበር/ህዳር 26/2007 በአዋጅ ቁጥር 544/1999 በማፀደቅና የሀገሪቱ የህግ አካል እንዲሆን በማድረግ ረገድ የራሷን ሚና ተጫውታለች፡፡ ይህ ደግሞ በ1987 ዓ.ም በወጣው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 9(4) መሰረት ኢትዮጵያ የምታፀድቃቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ የህግ አካል ተደርጎ እንደሚወሰድ የሚደነግግ በመሆኑ ስምምነቱ በዚሁ ድንጋጌ መሰረት የሀገሪቱ የህግ አካል ሆኖ በአስገዳጅነት ተካቷል፡፡

ይህን ትብብር ለማጠናከር ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የፀረ-ሙስና ስምምነቶችን በመፈራረምና እነዚህን ስምምነቶች በትብብር ተግባራዊ ለማድረግ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ አገራችንም ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽኖችን በመፈረሟ ምክኒያት በመድረኮች በንቃት እየተሳተፈች ትገኛለች፡፡ እነዚህ መድረኮችም ከሌሎች ልምድ ለመቅሰም፣ የራሷንም ተሞክሮ ለማካፈል አስችሏታል፡ ፡

# ቆይታ



## በአዲሱ ክልላችን በ2016 በጀት ዓመት በትውልድ የሥነምግባር ግንባታ እና በሙስና መከላከል ላይ የተሰሩ ተግባራት ለቀጣይ ሥራዎች አበረታች ናቸው!

**ኮሚሽነር ሶፎኒያስ ደስታ**

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሶፎኒያስ ደስታ በተጠናቀቀው የ2016 በጀት ዓመት በክልሉ የተከናወኑ ስራዎችን እና በቀጣይ ስለሚሰሩ ተግባራት ከፀረ-ሙስና ጋዜጣ ጋር ቆይታ አድርገዋል፡

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፦** በቅድሚያ ራስዎን ለአንባቢዎች ያስተዋውቁልን?

**ኮሚሽነር ሶፎኒያስ፦** ሶፎኒያስ ደስታ እባላለሁ፤ የደቡብ ኢትዮጲያ ክልላዊ መንግስት የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ነኝ፡፡

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፦** በበጀት አመቱ የተከናወኑ ዋና ዋና ስራዎች ምንድን ናቸው?

**ኮሚሽነር ሶፎኒያስ፦** ሥራዎችን በዘርፍ በዘርፍ ነዉ የሰራናቸዉ፡፡ በሥነምግባር ግንባታ ዘርፍ ትምህርትና ሥልጠና መስጠት ነዉ፡፡ ሌላኛው በሙስና የመከላከል ዘርፍ ዉስጥ ግን በርካታ ስራዎች ናቸው ያሉት፡፡ በሙስና መከላከል ላይ የተሰሩ ተግባራት በጣም አመርቂ ስራዎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ያህል ከ181 ሚሊዮን ብር በላይ የተመዘበረ ሀብት አስመልሰናል፡፡ የተመለሰዉን ሀብት እንዴት እናረጋግጣለን፣ የገንዘብ ጉድለት የታየበት ወይም አጥፍተዋል የተባሉትን ግለሰቦች ቀጥታ እንዲመልሱ ይጠየቃል፤ የሚመለሰው ገንዘብ ካርኒ ተቆርጦ ገቢ ይደረጋል፡፡ በዚህም ተመላሽነቱን የማረጋገጥ ስራ ይሰራል ማለት ነው፡፡

በዚህ በበጀት ዓመቱ የመጡ ጥቆማዎች 52 አካባቢ ናቸው፥ እነዚህ ጥቆማዎች ሙስና ተፈጽሞ ከሆነ በቀጥታ ለህግ እንዲቀርብ ነው የምናደርገው ለምሳሌ ያህል በቴክኒክና ሙያ ስር ከሚተዳደሩ ሁለቱ ኮሌጆች ላይ የማጣራት ስራ ሰርተን አንደኛው ላይ በጎፋ ዞን ቡልቂ



ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ በሚባል ከግንባታ ሥራ ጋር በተያያዘ 35 ሚሊየን ብር ማስመለስ ተችሏል። 15 ሚሊየኑ የተመዘበረ ሲሆን፣ 20 ሚሊየኑ ደግሞ ሊመዘበር ሲል ነው ከብሄራዊ ባንክ ትእዛዝ የተሰጠውን አግደን ንብረቱን ማዳን የቻልነው በድምሩ ከዚህ ግንባታ ሥራ 35 ሚሊየን የሚሆን የመንግስት ገንዘብ እንዳይጠፋ ጥንቃቄ አድርገናል፡፡ ጥፋቶቹ በኦዲተሮች መረጋገጣቸው የታወቀ በመሆኑ 16 የሚሆኑ ግለሰቦች ክስ ተመስርቶባቸው በቁጥጥር ስር የዋሉት ስድስቱ ብቻ ናቸው፥ ሌሎቹ እየተፈለጉ ይገኛሉ፡፡

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፦** በሙስና መከላከሉ ዘርፍ ጠንካራ ስራዎች እንደተሰሩ ገልጸዋል የሙስና ወንጀሎች በሚፈጸሙበት ወቅት እንደ ኮሚሽን ምን ዓይነት እርምጃ ይወሰዳል። የተወሰደስ ካለ ቢገልጹልኝ?

**ኮሚሽነር ሶፎኒያስ፦** በየ ዞኑ በጣም በርካታ ሰዎች ታስረዋል፡፡ በብዛት በክስ ሂደት ላይ ያሉም አሉ፣ የተፈረደባቸው እንዲሁ፥ እንደ ክልል ኮሚሽን በርካታ ስራዎች ሰርተናል። በዚህም 181 ሚሊዮን ብር የህዝብና የመንግስት ሀብት አስመልሰናል፡፡ ይህ ቀላል ገንዘብ አይደለም፥ መንግስት በርካታ ስራዎችን ሊያከናውንበት ይችላል፡፡

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፦** ክልሉ አዲስ እንደመቋቋሙ መጠን በርካታ ስራዎች ተሰርተውበታል፤ በነዚህ ጊዝያት ያጋጠሟችሁ ተግዳሮቶች ይኖራሉ?

**ኮሚሽነር ሶፎንያስ፦** የጎላ ችግር ባይገጥመንም መጠነኛ የሆነ ነገር አለ፤ ይህም ተጠርጣሪዎቹ በሚያዙበት ጊዜ ከሃገር ሃገር እየሸሹ፣ ከዞን ዞን፣ ከከተማ ከተማ እየጠፉ ያስቸገሩ ሲሆን፣ ይህም ካለን በጀት አንጻር የክልሉ ፖሊስም ተከታትሎ መያዝ አልቻለም፡፡ ይህ የቅንጅት ችግር ሳይሆን ከአቅም ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ሌላው ያለማጣራት ችግር ነው፡፡ ማረሚያ ቤቶች ላይ በምንሄድበት ጊዜ ፈቃደኛ ያለመሆን፣ ሰነዶችን የመደበቅ፣ ያለመተባበር የመሳሰሉ ችግሮች ናቸው ያሉት፡፡ እንደተባለው ሙስና ውስብስብ ስለሆነ እና የሚያስጠይቅ ስለሆነ ያጭበረበረ እና የሰረቀ ግለሰብ በጣም ይጠነቀቃል፡፡ በዚህም ማስረጃዎች ይሰውራሉ፤ በጉልበት በህግ እያስገደድን ነው የምንሰራው፡፡ መረጃ በሚከለክሉበት ወቅትም ኦዲተሮችን እየላክን እንዲያጣሩ እናደርጋለን፡፡ ሌላው የሎጅስቲክ/የበጀት እጥረት ገጥሞናል፡፡ ክልሉ አዲስ ስለነበረ በበጀት በጣም ተቸግረን ነበር፡፡ እናም በቀጣይ ከዚህ የተሻለ ስራ ማከናወን እንዲያስችለን በጀት ላይ ትኩረት እንዲሰጥ በዚህ አጋጣሚ ማሳሰብ እንወዳለን በተመሳሳይም የተሽከርካሪ ችግር ነበረብን፡፡ ከዚህ ውጭ ግንዛቤ የፈጠርንላቸው ሰዎች ጥቆማዎችን ያመጣሉ፥ በተረፈ ከዚህ የበለጠ መስራት አለብን ብለን እናምናለን። ሌላው የጠቋሚዎች እጥረት አለ፡፡ አንድ ክልል ውስጥ 52 ጥቆማ በጣም ትንሽ ነው ብዬ አስባለሁ ከዚህ የበለጠ ጥቆማዎችን ለመቀበል የተለያዩ ግንዛቤዎችን የሚፈጥሩ ስራዎችን እንሰራለን ብዬ አስባለሁ። የበጀትና የተሽከርካሪ እጥረት እየተቀረፈ ከሄደ በቀጣይ የ2017 በጀት አመት የተሻለ ስራ እንሰራለን ብዬ አስባለሁ።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፦** በተጠናቀቀው በጀት አመት በሀብት ማሳወቅና ማስመዝገብ፣ በሙስና መከላከል፣ በሥነምግባር ግንባታ ስልጠናዎችና የግንዛቤ ፈጠራ ስራዎችን ከመስራት አንጻር የክልሉ የሥራ አፈጻጸም ምን ይመስላል?

**ኮሚሽነር ሶፎንያስ፦** ከሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ጋር በተያያዘ ወደ 130,000 ሃብት ማሳዎቅና ማስመዝገብ የሚገባው የመንግስት ተሿሚና ሠራተኛ እንዲሁም ተመራጭ እንዳለ ለይተናል። ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ 6,022 ከክልል ጀምሮ እስከ ወረዳ አስተዳደር ድረስ ያሉ አመራሮች ናቸው፡፡ ይህን ለማስመዝገብ ካቀድን በኂላ ያደረግነው ከ6,000 ውስጥ እስከ ሚያዚያ ወር/ 4ኛ ሩብ አመት 3,000 የሀብት ማሳወቅና መመዝገብ አለበት ብለን ነው ያቀድነው በዚሁ መሰረት ሶስት ሺውን አስመዝግበናል፡፡ ቀሪ ሶስት ሺ ሃያ ሁለቱን ደግሞ በሚቀጥለው በጀት አመት አሳትመን ወደ ስራ እንገባለን፡፡ ወደ ፒዲ ኤፍ

ከመስራት ወደ ዲጂታላይዝድ የሚያስገባ አሰራር ስላልተዘረጋ በሃርድ ኮፒ ከሰራን በኋላ ወደሶፍት ኮፒ ቀይረን ለመስራት አስበናል ከዚህ ውጪ ለፍትህ አካላትና አመራሮች፣ ለዳይሬክተሮችና ለፈጻሚዎች በሶስት ዙር ስለ ሃብት ማሳወቅና ምዝገባ አዋጅ ትምህርት ሰጥተናል አሰራሩ በምን መልኩ ነው መሰራት ያለበት የሚለውን ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተን ውጤታማ ስራ እየሰራን ነው፡፡ ቀድሞ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች የተመዘገቡ የሃብት ምዝገባ ቅጾች በሙሉ ስካን ተደርገው የተቀመጡ ዶክመንቶችም አሉን፡

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** በሀገራዊ የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ረቂቅ ፖሊሲ ላይ እንደ ክልል በምን መልኩ የግብዓት ማሰባሰቢያ የውይይት መድረክ አካሄዳችሁ

**ኮሚሽነር ሶፎንያስ፡-** በሀገራዊ የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ረቂቅ ፖሊሲን በተመለከተ በቅድሚያ ለፖሊሲው ግብዓት የሚሰጡ ባለሙያዎችን ልከን ነበር፡፡ በመቀጠልም በማኔጅመንት ከተወያየን በኋላ ከኮሚሽናችን ሰራተኞች ጋር መወያየት ችለናል፡፡ በቀጣይም ከባለድርሻ አካላት ጋር ተወያይተናል፡፡ በተለይም ከትምህርት ተቋማት ከኛ ጋር ተቀራርበው የሚሰሩ፣ በትምህርት ሊያዳብሩ ከሚችሉ ከትምህርት ቤቶችና ኮሌጆች ከሥነምግባር ቡድን መሪዎች ጋር በመሆን ረቂቅ ፖሊሲውን በደንብ አዳብረን ለፌደራል የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በመላክ የራሳችንን አስተዋጽኦ አበርክተናል

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** በበጀት አመቱ ሊከወኑ ታቅደው ያልተጠናቀቁ ስራዎች አሉ ካሉ በምን ምክንያት

**ኮሚሽነር ሶፎንያስ** ለሚቀጥለው በጀት አመት የተሸጋገረው ሥራ ከሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ጋር ተያይዞ ያለው ሥራ ሲሆን፥ የአመራሩን ግማሽ የሚያህል የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ቀሪ ሥራ በበጀት እጥረት ምክንያት ወደ ሚቀጥለው በጀት አመት ተሸጋግሯል ሌላው አሁን ከመጡ ጥቆማዎች የተወሰኑ በምርመራ ሂደት ላይ ይገኛሉ፥ እነዚህ ጥቆማዎች በሚቀጥለው በጀት አመት የሚሰሩ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ ቀሪ ስራዎችን በእቅድ አይተንና የቀሩትን ስራዎች ከልሰን በ2017 በጀት ዓመት አጠናክረን የምንሰራ ይሆናል፡፡

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- የቀጣይ በጀት ዓመት ዝግጅት ምን ይመስላል?

**ኮሚሽነር ሶፎንያስ፡-** ለ2017 በጀት ዓመት በጀት በደንብ ይመደብልናል ብለን እናስባለን፡፡ አሁን ላይ የተጠና አደረጃጀት አለ፤ እሱን በማስተካከል ወደስራ እንገባለን ብዬ አስባለሁ፡፡ ስለሆነም ስራዎችን ከፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽንና ከሌሎች አጋር ተቋማት ጋር ተቀናጅተን እንሰራለን፡፡ ተጨማሪ የሰው ሃይል ለሚያስፈልገው ዘርፍ እያየን በመቅጠርና በማሟላት ስራዎችን በወኔ እንሰራለን ብለን ተስፋ እናደርጋለን

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** በመጨረሻ መጨመር የሚፈልጉት ሃሳብ ካለ?

**ኮሚሽነር ሶፎንያስ፡-** ሁሉም ሰው ሙስና የሃገሪቱ የእድገት ፀር በመሆን ልማትን እንደሚጎዳ በመገንዘብ በደቡብ ኢት/ያ ክልላዊ መንግስት ስር የሚገኝ ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛም ሆነ ነዋሪ የሙስና ወንጀልን በመጠቆም እና በማጋለጥ ሃገራዊ ድርሻውን እንዲወጣ፡፡ ሙስናን በጋራ ብንዋጋ መልካም ነው እያልኩ፥ ከሌሎች ባለ ድርሻ አካላት ጋር እያደረግን ያለውን የጋራ ስራ በማስቀጠልና ከማህበረሰቡ ጋር በመቀናጀት እንድንሰራ ጥሪ አቀርባለሁ፡

**አመሰግናለሁ!**

# የ10ኛው የኢትዮጵያ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ትስስር ጉባኤ

## የአቋም መግለጫ

ሙስና ልማትና ዕድገትን የሚያደናቅፍ አለም አቀፍ ወንጀል ነው፡፡ ችግሩ በሀገራችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና የፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ላይ የራሱ አሉታዊ ተፅዕኖ በማስከተል ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ለፀረ-ሙስና ትግል ሁሉም የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖችና የሚመለከተቻው ባላድርሻ አካላት ተገቢውን ጉልህ ድርሻ ሊወጡ ይገባል፡፡ ከዚህ አኳያ በ2016 በጀት ዓመት ለሙስና መንስኤ በሆኑ የሥነምግባር ችግሮች ላይ ለውጥ የሚያመጡ ሥልጠናዎች በመስጠት፣ በተቋማት ለሙስና እና ብልሹ አሠራር በር የሚከፍቱ አሠራሮችን መዝጋት የሚያስችሉ የማሻሻያ ምክረ ኃሳቦችን በማመንጨትና የመፍትሄ ሃሳቦች ተግባራዊነትን በመከታተል፣ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እና በትስስር በመስራት፣ የአስቸኳይ ሙስና መከላል ተግባራትን በማከናወን እንዲሁም በሙስና ወንጀል የህግ ማስከበር ሥራዎችን ከፍትህ አካላት ጋር በመቀናጀት ለትግሉ ስኬት የሚያግዙ ተግባራትን በማከናወን አበረታች ውጤቶችን አስመዝግበናል፡፡

ስለሆነም እኛ በፌዴራል፣ በክልልና በከተማ አስተዳደር የምንገኝ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች በ2017 በጀት ዓመትም ከሌሎች የፀረ-ሙስና ትግሉ አጋዥ ከሆኑ የባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የተለያዩ የአሠራርና አደረጃጀት ሪፎርም ሥራዎችን በመሥራትና አስቻይ ሁኔታ በመፍጠር፣ ትውልድን በሥነምግባር የማነጽ፣ ሙስናን የሚፀየፍ እና በጽናት የሚታገል ህብረተሰብ የማብዛት ሥራዎችን በማከናወን እና በተቋማት ውስጥ የቅድመ-ሙስና መከላከል ሥራዎችን በስፋት በመሥራት የግልጽነትና ተጠያቂነትን አሠራር በማስፈን የሀገሪቱን የፀረ-ሙስና ትግል እንቅስቃሴ ውጤታማ ለማድረግ እንዲያስችለን ይህን የጋራ አቋም መግለጫ አውጥተናል፡፡

1. የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች በአዋጅ ከተሰጣቸው ተልዕኮዎች አንዱ በሥነምግባር የተገነባ፣ ሙስናን የሚፀየፍና የሚያጋልጥ አመራር፣ የሥራ ኃላፊና ሠራተኛ እንዲሁም ማህበሰብ እንዲፈጠር ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም በቀጣይ የ2017 በጀት ዓመት ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር ዘርፍ ተኮር ስልጠናዎችን በስፋት በማከናወን በመንግስት ተቋማት፣ በህዝባዊ ድርጅቶች እና በየደረጃው በሚገኙ የህብረተሰብ አካላት ሥነምግባራዊነትን እንዲላበሱና ሙስና እና ብልሹ አሠራርን መከላከል የሚያስችል አቅም እንዲያጎለብቱ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎች በስፋት ለማከናወን ቃል እንገባለን!

2. የሥነምግባር መከታተያ አደረጃጀትን በማጠናከር በዘርፍና በተጠሪ ተቋማት የሙስና ስጋትን ከመከላከል አንፃር ፋይዳው ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም ባለፈው በጀት ዓመት የተስተዋሉ ችግሮችን በመቅረፍ በቀጣዩ በጀት ዓመት የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በሥነምግባር ታንፀው ኃላፊነታቸውን በትጋት እንዲወጡ ለማስቻልና የመፈጸም ብቃታቸውን ለማሳደግ ተገቢውን የክትትልና ድጋፍ ለማከናወን ቃል እንገባለን!

3. የፀረ-ሙስና ትግል ያለ ህብረተሰብ ተሳትፎ ሊሳካ እንደማይችል ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ህብረተሰቡ በፀረ-ሙስና ትግል በንቃት በመሳተፍና ሚናውን በተገቢው በመወጣት እንደሀገር የተጀመረውን የፀረ-ሙስና ትግል ውጤታማ ለማድረግ የፀረ-ሙስና ትግል እንቅስቃሴ፣ መልዕክቶችንና መረጃዎችን በወቅቱ ለህብረተሰቡ ተደራሽ በማድረግና ግንዛቤ በመፍጠር ህብረተሰቡን ለፀረ-ሙስና ትግሉ በሰፊው ለማነሳሳት ተግተን ለመሥራት ቃል እንገባለን!

4. የመንግሥት አሠራሮች ግልፅና ተጠያቂነት እንዲኖራቸው የሙስና መከላከል ጥናት የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም በመንግስት መሥሪያ ቤቶች፣ በልማት ድርጅቶችና ህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ለሙስና እና ብልሹ አሠራር ቀዳዳ የሚከፍቱ አሠራሮችን በትኩረት በመለየት የማሻሻያ ምክረ ሀሳብ በማቅረብና የመፍትሄ ሀሳቦች ተግባራዊነቱን በመከታተል ተገቢውን ውጤት ለማስመዝገብ ተግተን ለመሥራት ቃል እንገባለን፡፡

5. ሙስና ከመፈጸሙ በፊት በአስቸኳይ ሙስና መከላከል ሥራዎች የሙስና ወንጀልን የማጨናገፍ ተግባር ለፀረ-ሙስና ትግሉ ፋይዳው ትልቅ ነው፡፡ በመሆኑም ዜጎች ያገኙትንና ያወቁትን መረጃና ማስረጃ እንዲጠቀሙ ግንዛቤ በመፍጠርና ለመረጃ ቅበላ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የቀረቡ ጥቆማዎችን በመቀበል ወደ ሙስና ድርጊት ከመለወጡ በፊት እንዲቋረጥ በማድረግ እና በተፈጸሙ የሙስና ወንጀል ድርጊቶች ላይ ተገቢውን የህግ ማስከበር እርምጃ እንዲወሰድ ለፍትህ አካላት በማስተላለፍ እንዲሁም ውጤቱንም በመከታተል በመንግስት ተቋማት ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን በማድረግ የፀረ-ሙስና ትግሉን ውጤታማ ለማድረግ ቃል እንገባለን!

6. በመንግስት ተቋማትና በህዝባዊ ድርጅቶች ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን አልፎም አለአግባብ የተፈራ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ለማጋለጥ እና የተዘመበረ ሀብትን ከማስመለስ አንፃር ውጤታማ የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ሥርዓት ትግበራ ወሳኝ ነው፡፡ በመሆኑም በህግ ሀብታቸውን ማስመዝገብ ግዴታ ያለባቸው አመራሮች፣ ሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በግልጽ በተቀመጠ የጊዜ ገደብ ውስጥ ሀብትና የገቢ ምንጫውን እንዲያሳውቁና እንዲያስመዘግቡ በቁርጠኝነት ኃላፊነታችንን ለመወጣት ቃል እንገባለን!

7. የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች እንቅስቃሴ ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እንዲከናወን በየጊዜው አስቻይ ሁኔታ የሚፈጥሩ ማሻሻያዎችን በስፋት ለማከናዎን ቃል እንገባለን!

8. በመጨረሻም እኛ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች፥ በሀገርና በየደረጃው እስከታችኛው የሀገሪቱ የአስተዳደር እርከኖች የፀረ-ሙስና ትግሉን በውጤታማነት ከመምራት አኳያ ቃላችንን በተግባር በመለወጥ በ2017 በጀት ዓመት የፀረ-ሙስና ትግሉ ላይ በዓይነቱ የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ በቁርጠኝነትና በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት ለመንቀሳቀስ ቃል እንገባለን፡፡

**ሙስና የጋራ ጠላታችን ነው፤ በህብረት እንታገል!**

ሰኔ 25/2016 ዓ.ም አዳማ

**ከሙስና የፀዳች ኢትዮጵያ!**

# ሳይቃጠል በቅጠል

## በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ በግዥ አፈጻጸም ሂደት የሚታዩ ክፍተቶች

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ውስጥ የሚታዩ የአሰራር ክፍተቶችን ለመዝጋት የችግሮችና መንስኤዎች በጥናት በመለየት ለሚመለከተው ተቋም የመፍትሄ ሃሳብ ማቅረብና ተግባራዊነቱን በማረጋገጥ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ከሚጠቀምባቸው ስልቶች አንዱ ነው፡፡ ይህ ፅሁፍ ኮሚሽኑ በተለይ በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ በግዥ አፈጻጸም ሂደት የሚታዩት ክፍተቶችን ለመለየት ባካሄደው የአስቸኳይ የሙስና ጥናት ላይ የሚያተኩር ሲሆን፣ በጥናቱ የተገኙ ውጤቶችን እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ተቋም በመገኘት ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ሰነዶችና መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በመመልከት እና ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍል ኃላፊዎች ጋር ውይይት በማድረግ ጥናቱ ተካሄዷል፡፡

በዚህም በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ በተካሄደው የማጣራት ሂደት የ2016 ዓ.ም የስልጠና ዘመን የአላቂና የስፖርት ስልጠና ትጥቅ እና ቁሳቁስ ግዥ ፍላጎት ሰነድ፣ የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ለስፖርት አካዳሚ የላከውን የኦዲት ሪፖርት ሰነድ፣ የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ በቀን 26/02/2016 ለአስመጪ ድርጅት ያስገባውን የቅርጫት ኳስ ቦርድ እንዲወስድ ያሳወቀበት ደብዳቤ እና የኢትዮጵያ ቅርጫት ኳስ ፌዴሬሽን የቴክኒካል ምርመራ ሪፖርት ሰነድ አጥኚዎች ተመልክተዋል፡፡

አጥኚው ቡድን የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ቴክኒክ ኮሚቴው የሰጠውን ውሳኔ በመጠራጠር አካዳሚው ታህሳስ 4/2016 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ቅርጫት ኳስ ፌዴሬሽን የቴክኒክ ምርመራ የሚያደርጉ ባለሙያዎች እንዲልኩ በጠየቀው መሰረት የቴክኒክ ምርመራ አድርገው የቀረበው ቅርጫት ኳስ ተንቀሳቃሽ ቦርድ በጨረታ ሰነዱ በቀረበው መመዘኛ መስፈርት ያላሟላ መሆኑን ታህሳስ 9/2016 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ያሳወቀ ከመሆኑም ባሻገር ተጠቃሚ የስራ ክፍሉ እቃው ደረጃውን የጠበቀ ያለመሆኑ በተደጋጋሚ የገለፀ በመሆኑ በአካዳሚው የጥራት ኮሚቴ የተሰጠው ማረጋገጫ አጠራጣሪ ሁኔታ መፍጠሩን የጥናት ቡድኑ ተመልክቷል፡ ፡እንዲሁም አጥኚው ቡድን የአካዳሚው የቴክኒክ ኮሚቴ ጥቅምት 6/2016 ዓ.ም በጨረታው አሸናፊ ለነበረው ተጫራች (አስተፍስህ አስመጪና ላኪ ኃ/የ/ግል ማህበር) ያቀረበው ቅርጫት ኳስ ተንቀሳቃሽ ቦርድ በግዥ ሰነዱ ላይ በቀረበው ዝርዝር መግለጫ ስፔሲፊኬሽን መሰረት ስለመሆኑ ያረጋገጡ ቢሆንም በሙሉ የኮሚቴ አባላት አለመፅደቁ እና ቀሪ የነበረው የቴክኒክ ኮሚቴ አባል በምን ምክንያት እንደቀረ የተያዘ ቃለ ጉባኤ የሌለ መሆኑ እና በአካዳሚው የቅርጫት ኳስ ቦርድ ለመግዛት ተይዞ የነበረው ግምታዊ ዋጋ ብር 900,000 (ዘጠኝ መቶ ሺህ ብር) እና አቅራቢው ያቀረበው ብር 4,800,000 (አራት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺህ) ዋጋ ከፍተኛ ልዩነት የታየና የገበያ ዋጋ ጥናት ያልተደረገ በመሆኑ የጨረታው አሸናፊ ተጫራች ዋጋ አጠራጣሪ ሁኔታ መፍጠሩን የጥናት ቡድኑ ማረጋገጥ እንደቻለ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በተጨማሪም አቅራቢው ድርጅት ያስገባውን የቅርጫት ኳስ ተንቀሳቃሽ ቦርድ በተገባው የግዥ ውል ላይ በተቀመጠው ዝርዝር መግለጫ መሰረት ስላልቀረበ ንብረታችሁን እንድትወስዱ የሚል ደብዳቤ ጥቅምት 26/2016 ዓ.ም የተገለፀለት ቢሆንም ድርጅቱ የቴክኒክ ኮሚቴ አረጋግጦልኛል በማለት ክፍያ እንዲፈፀምለት ከመጠየቁ በተጨማሪ በፍርድ ቤት ክስ ያቀረበ ስለመሆኑ እንዲሁም አቅራቢው ድርጅት ያቀረበው የቅርጫት ኳስ ተንቀሳቃሽ ቦርድ የምርት ስምና እቃዎች እና አገልግሎቶች የአጠቃቀም ማኑዋል አለመኖሩን በተደረገው የመስክ ምልከታና ከተጠቃሚ ሥራ ክፍል ጋር በተደረገው ውይይት የጥናት ቡድኑ ማረጋገጥ ችሏል፡፡

**አቅራቢው ድርጅት ያቀረበው የቅርጫት ኳስ ተንቀሳቃሽ ቦርድ የምርት ስምና እቃዎች እና አገልግሎቶች የአጠቃቀም ማኑዋል አለመኖሩን በተደረገው የመስክ ምልከታና ከተጠቃሚ ሥራ ክፍል ጋር በተደረገው ውይይት የጥናት ቡድኑ ማረጋገጥ ችሏል፡፡**

በመሆኑም የጥናት ቡድኑ የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ የስፖርት ትጥቅ ግብዓቶችን ለመግዛት በቀን 29/9/2015 ዓ.ም ባወጣው ግልፅ ጨረታ ላይ የቅርጫት ኳስ ተንቀሳቃሽ ቦርድ ግዥ የተወዳደረው አቅራቢ አንድ ብቻ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሰጠው ዋጋ የገበያ ዋጋ ስለመሆኑ ሳይረጋገጥ ውል የተገባበት ሁኔታ እንደገና የሚታይ ቢሆን እንዲሁም የተጠቀሰው የቅርጫት ኳስ ተንቀሳቃሽ ቦርድ ግዥ የቀረበው እቃ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ያለመሆኑ የተለያዩ አካላት ያረጋገጡት ከመሆኑም በላይ የአካዳሚው የቴክኒክ ኮሚቴ በገለልተኛ አካል ታይቶ አስተዳደራዊ የእርምት እርምጃ እንዲወስድ የሚል ምክረ-ሃሳብ አጥኚው ቡድን አቅርቧል፡፡

# ከሙስና ምርመራ ማህደር



በዚህ አምድ የተለያዩ ከሙስና እና ብልሹ አሠራር ጋር በተያያዘ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተከናወኑና ለህብረተሰቡ ከፍተኛ እውቀትና እውነተኛ መረጃ ይሰጣሉ ተብለው የሚታመኑና በሙስና ወንጀል የተመዘበረ የሀገር፣ የህዝብና የመንግስት ሀብት በማስመለስ ዙሪያ የተከናወኑ ተግባራት እና ግንዛቤ የሚፈጥሩ ዋና ዋና ጉዳዮች አጠር ተደርገው የሚቀርቡበት ነው፡፡

በመሆኑም ከአፍሪካ ኅብረት ሒሳብ 6 ሚሊየን 50 ሺህ ዶላር የምዝበራ ሙከራ ጋር ተያይዞ በተከሰሱት በእነ ቀሲስ በላይ መኮንን መዝገብ ላይ ዐቃቤ ሕግ ምስክር አሰምቷል፡፡ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችን ቃል የሰማው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ነው፡፡

የፍትሕ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ በእነ ቄስ በላይ መኮንን፣ በግብርና ኢንቨስትመንት በተሰማራው ኢያሱ እንዳለ ወ/መስቀል፣ በኮሚሽን ስራ በተሰማራው በረከት ሙላቱ ጃፋር፣ ዓለምገና ሳሙኤል ዲንሳ እና የኒሞና ንግድ ስራ ኃላ/የተ/የግል ማኅበር ስራ አስኪያጅ አበራ መርጋ ተስፋዬ ላይ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ ቁጥር 32 ንዑስ ቁጥር 1 (ሀ) እና የሙስና ወንጀሎች ለመደንገግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 32 ንዑስ ቁጥር 2 እና ንዑስ ቁጥር 3 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ እና በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ቁጥር 382 ንዑስ ቁጥር 1 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ከአፍሪካ ኅብረት የክፍያ ትዕዛዝ ባልተሰጠበት ሁኔታ ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ ቁጥር ለተከሰሱ ግለሰቦች የተለያየ የዶላር መጠን ክፍያ እንዲፈጸምላቸው የሚል አጠቃላይ የ6 ሚሊየን 50 ሺህ ዶላር ሀሰተኛ የክፍያ ሰነድ በአንደኛ ተከሳሽ መቅረቡን ጠቅሶ በሁሉም ግለሰቦች ላይ ከባድ የማታለል ሙስና ወንጀል ክስ መመስረቱ ይታወሳል፡፡

ከ1ኛ እስከ 3ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ችሎት የቀረቡና የክስ ዝርዝሩ እንዲደርሳቸው የተደረገ ሲሆን፣ 4ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች በአድራሻቸው ባለመገኘታቸውና በተደጋጋሚ ቀጠሮ ባለመቅረባቸው ለጊዜው ክሳቸው እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡ ችሎት የቀረቡት ተከሳሾችም ክሱ እንዲሻሻልላቸው ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ ክስ መቃወሚያ ነጥቦችን ፍርድ ቤቱ መርምሮ ወደፊት በማስረጃ እንደሚጣራ በማመላከት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ በክሱ ላይ የተጠቀሰውን የወንጀል ድርጊት አለመፈጸማቸውን ጠቅሰው፤ ተከሳሾቹ የዕምነት ክህደት ቃላቸውን መስጠታቸውን ተከትሎም ዐቃቤ ሕግ ሶስት ምስክሮችን አቅርቧል፡፡

ቀረበ ስለተባለው የክፍያ ሰነድና ተያያዥ ጉዳዮችም የምስክር ጭብጥ በማስመዝገብ በዋና ጥያቄ የምስክሮቹን ቃል አሰምቷል፡፡ የተከሳሽ ጠበቆችም መስቀለኛ ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን፣ በፍርድ ቤቱ የማጣሪያ ጥያቄ ተነስቶ ከምስክሮች መልስ ተሰጥቶበታል፡፡ ፍርድ ቤቱም የዐቃቤ ሕግ ምስክር ቃልን መርምሮ ብይን ለመስጠት ለሐምሌ 18 ቀን 2016 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡

በሌላ የሙስና ወንጀል መረጃ በ18 የንግድ ዘርፎች ፈቃድ በመውሰድ ግብይት ሳይፈጸም ደረሰኝ በመሸጥ ከ3 ቢሊየን ብር በላይ የንግድ ትርፍና የተጨማሪ እሴት ታክስ ጉዳት በማድረስ ወንጀል የተጠረጠሩ ግለሰቦች ተከሰዋል፡፡ የፍትሕ ሚኒስቴር የኢኮኖሚ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ ማቲዮስ ተስፋዬ (በሀሰተኛ ስሙ ሀይሉ አባተ)፣ ቢኒያም ሙሉነህ፣ መኩሪያ አለሙ እና ዮሃንስ አለማየሁ በተባሉ 4 ግለሰቦች ላይ በየተሳትፎ ደረጃቸው ጠቅሶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ተደራራቢ ክሶችን አቅርቦባቸዋል፡፡

በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ ቁጥር 1 ሀ እና ለ እንዲሁም የሙስና ወንጀልን ለመከላከል የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 1 እና 2 ስር የተመለከተው ድንጋጌ እና የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 በተለይም በዚሁ በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር1150/2011 አንቀጽ 49 ንዑስ ቁጥር 3 ስር በተጨማሪ የታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008 አንቀጽ 116፣118 ስር የተመላከቱ ድንጋጌዎችን መተላለፍ የሚሉ ተደራራቢ ክሶችን ነው ዐቃቤ ሕግ ያቀረበባቸው፡፡

በቀረበው ክስ ላይ 1ኛ ተከሳሽ በየካቲት ወር 2014 ዓ.ም በአዲስ አበባ ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 3 ልዩ ቦታው አዲሱ አስፓልት እየተባለ በሚጠራው አካባቢ በሀሰተኛ ስሙ ሀብታሙ ማሞ ለማ ትክክለኛ ስሙ መራዊ ሰለሞን ከበደ የተባለ ግለሰብን ስራ እንስራ በማለት በማሳመን፣ የግለሰቡን ፎቶ አስነስቶ በየካ ክ/ከ ወረዳ 6 ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ቅርጫፍ ጽ/ቤት የሚል ፎቶ ያልተለጠፈበት ሀሰተኛ መታወቂያ አዘጋጅቶ በሀብታሙ ማሞ ለማ ስም በተለያዩ የንግድ ዘርፎች 18 የንግድ ፍቃድ በማውጣት በመጋቢት 11 ቀን 2015 ዓ.ም ደግሞ ከዚህ ሀሰተኛ መታወቂያ ተዘጋጅቶ ንግድ ፈቃድ በስሙ ከወጣለት ሀብታሙ ማሞ ውክልና የተሰጠው በማስመሰል ከሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ቅርጫፍ 12 ጽ/ቤት የተሰጠው በማስመሰል ሀሰተኛ የውክልና ሰነድ በማቅረብ ከአንባሰል ንግድ ስራዎች ኃ/የተ/የግል ድርጅት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ በመውሰድ ደረሰኞችን ለተለያዩ ነጋዴዎች በሽያጭ ሲያቀርብ እንደነበር በክስ ዝርዝሩ ተጠቅሷል፡፡

በዚህም 2 ቢሊየን 627 ሚሊየን 541ሺህ 457 ብር ከ41 ሳንቲም የንግድ ትርፍ እና 1 ቢሊየን 128 ሚሊየን 267 ሺህ 803 ብር ከ03 ሳንቲም የተጨማሪ እሴት ታክስ በአጠቃላይ ከ3 ቢሊየን ብር በላይ በመንግስት ላይ ጉዳት እንዲደርስ መደረጉ በክሱ ተጠቅሷል፡፡

ሌሎች ተከሳሾችም በየደረጃው የንግድ ትርፍና የተጨማሪ እሴት ታክስ ለማጭበርበር በማሰብ ምንም አይነት የዕቃ ሽያጭ ሳይከናወን የሽያጭ ደረሰኞችን የሚገዙ ነጋዴዎች በማፈላለግና በማገናኘት ደረጃ ተሳትፎ እንዳላቸው ተመላክቷል፡፡ ስለሆነም በዋና ወንጀል አድራጊት፣ ተካፋይ በመሆን ከንግድ ስራ ውጤት ተጠቃሚ ባልሆነ ሰው ስም ንግድ ፈቃድ ማውጣትና ንግድ ስራ መስራት እንዲሁም ግብይት ሳይፈጸም ደረሰኝ መስጠት ወንጀል ተከሰዋል፡፡ ይህ የክስ ዝርዝር ለተከሳሾች እንዲደርስ ከተደረገ በኋላ ከዚህ በፊት በነበረ ቀጠሮ የዋስትና መብታቸው እንዲከበር በጠየቁት መሰረት ከዐቃቤ ሕግ ጋር ክርክር ተደርጓል፡፡

ፍርድ ቤቱ ክርክሩን መርምሮ በዕለቱ በዋለው ችሎት አንደኛ ተከሳሽ ከቀረበበት የክስ ተደራራቢነትና ከደረሰው ጉዳት አንጻር የዋስትና ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ በማረሚያ ቤት ሆኖ ጉዳዩን እንዲከታተል ታዝዟል፡፡ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ግን ካለቸው ተሳትፎ እና አግኝተዋል ከተባለው ጥቅም አነስተኛ መሆን አንጻር ከግምት ውስጥ በማስገባት ፍርድ ቤቱ የ450 ሺህ ብር ዋስትና አስይዘው ከእስር እንዲፈቱ እና ከሀገር እንዳይወጡ እግድ እንዲጣል ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ የ4ኛ ተከሳሽን ክስ በተመለከተም ቀደም ሲል በ250 ሺህ ብር ዋስትና ከእስር እንዲፈታ እንደተፈቀደለት ተጠቁሟል፡፡ ፍርድ ቤቱ የተከሳሾችን የክስ መቃወሚያ ከቀጠሮ በፊት በጽ/ቤት እንዲያቀርቡ በማለት በክስ መቃወሚያው ላይ ብይን ለመስጠት ለሐምሌ 8 ቀን 2016 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡

# ኪነ-ጥበብ

## ‹‹ አለማፈር ››

ከራስ ባልሆነ ጌጥ፣ በተውሶ ደስታ፤
ስጋ ተመቻችታ፣
ቅን ህሊና ከስታ፣
በሌላው ወዝ ግረት፣ እጅ እያቆሸሹ፤
ከቅጥፈት ተዛምደው፣ ከሀቅ እየሸሹ፤
በይምሰል ማንነት፣ ከራስ እየዋሹ፤
ገጽታን አብሰው፣ ውስጥ እያጠለሹ፤
በታሪክ ጠባሳ፣ መልክ እያበላሹ፤
ሰው ለመባል ክብር፣ ከሆነ ምላሹ።
እንደ ጠራ ውሀ፣ ከአለት መሀል ፈልቆ፤
መኖር አለመኖር፣ ካልተገኘ ልቆ፤
በታወረ እሳቤ፣ ተስቦ በስጋ፤
በተራ ቁስ ሽቀጥ፣ በረከሰ ዋጋ፤
የታቹ ተከፍቶ፣ ላዩ የተዘጋ፤
ከመባል ሙሰኛ፣ እምነት አልባ ዜጋ።
ካልዘሩት ማሳ ላይ፣ ዘር እየተመኙ፤
በጉቦ በምልጃ፣ ባህር እየዋኙ፤
ለአፈር ስጋ አድልቶ፣ ነፍስን በቁም ገድሎ፤
አሽቆልቁሎ ወርዶ፣ ከሙሉነት ጎድሎ፤
በጭላንጭል ተስፋ፣ በጭላጭ ማንነት፤
ባልተረገጠ እርካብ፣ ባልተጨበጠ እውነት፤
በእብቅ በእንክርዳድ፣ ቁና ከመስፈር፤
አለመኖር መልካም፣ ወይ ቀድሞ አለማፈር።

# መልካም ዜና

## የእጅ ስልክ ባለቤቱን በማፈላለግ በፖሊስ በኩል ያስረከበው የድሬድዋ ከተማ ወጣት ምስጋና ተቸረው።

የሰላም ታክሲ አሽከርካሪዎች ማህበር አባል የሆነው የፎርስ ሾፌር ወጣት አብዲ ኑር ኡስማን የሰሌዳ ቁጥሩ ድሬ ኮድ 1,12624 በሆነው ፎርስ መደበኛ ስራውን ከመልካጀብዱ ባቡር ጣቢያ ወደ ፖሊስ መሬት በማከናወን ላይ ሳለ በፎርሰ ውስጥ ተሳፍሮ የነበረው እና የጅቡቲ ዜግነት ያለው መሐዲ መሐመድ በፎርሱ ላይ ረስቶ የወረደውን የእጅ ስልክ የተመለከተው አብዲ ኑር የዋጋ ግምቱ ሀያ ስምንት ሺህ ብር የሚያወጣ እና ሲም ካርድ የሌለው ስልክ ቀፎ በመሆኑ ለመልካጀብጁ ፖሊስ ጣቢያ ወስዶ በማስረከብ እና ንብረቱ የጠፋበትን ግለሰብ ከአንድ ሳምንት በላይ በማፈላለግ ንብረቱ እንዲመለስ ያደረገ ሲሆን፥ ንብረቱ ጠፍቶ የተገኘለት መሐዲ መሐመድ በሰጠው አስተያየት ንብረቱ በመገኘቱ በጣም ደስተኛ መሆኑን ገልፆ አሽከርካሪው ላሳየው ቀናነት እና ታማኝነት ምስጋናውን አቅርቧል።

ንብረቱን ለባለቤቱ ያስረከበው ወጣት አብዲ ኑር ዑስማን በበኩሉ በሰጠው አስተያየት ባከናወነው መልካም ተግባር ደስተኛ መሆኑን ገልጾ፥ እንደ ማህበር ከመልካጀብዱ ፖሊስ ጣቢያ ጋር በጋራ እንደሚሰራ ተናግሯል። የሰላም አሽከርካሪዎች ሊቀመንበር ወጣት በሐር ካሚል በበኩሉ ባስተላለፈው መልዕክት እንደማህበር በሚያከናውኗቸው ተግባራት ታማኝነትንና ቅንነትን እንደሚያስቀድሙ ተናግረው፥ በቀጣይም ከፖሊሰ ጋር ተባብረው ለመስራት ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል።

የድሬድዋ ከተማ አስተዳደር የመልካ ጀብዱ ፖሊስ ጣቢያ አዛዥ ዋና ኢንስፔክተር ሻምበል ተካልኝ በበኩላቸው ወጣቱ ያከናወነው ተግባር የሚያስመሰግን መሆኑን ገልፀው፥ የሰላም አሽከርካሪዎች ማህበር መሰል አርዓያነት ያለው ተግባር በተደጋጋሚ እያከናወኑ የሚገኙ መሆኑን ጠቅሰዋል። በቀጣይም ከፖሊስ ጋር ተባብረው የሚያከናውኗቸውን ተግባራት አጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባ ጨምረው ተናግረዋል።

